# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 277 ሰኔ 7 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ጣሊያን ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ግንኙነት አጠናክራ እንደምትቀጥል አስታወቀች

## - ኢትዮጵያና ጣሊያን የአንድ ነጥብ 23 ቢሊዮን ብር የብድር ስምምነት ተፈራርመዋል

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- ጣሊያን ከኢትዮጵያ ጋር ያላትን ዘርፈ ብዙ ግንኙነት አጠናክራ እንደምትቀጥል አስታወቀች፡፡ ኢትዮጵያና ጣሊያን አነስተኛ ወለድ ያለው የአንድ ነጥብ 23 ቢሊዮን ብር የብድር ስምምነት ትናንትና ተፈራርመዋል፡፡

የብድር ስምምነቱን የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሺዴና የጣሊያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሉዊጂ ዲ ማዮ ተፈራርመዋል፡፡

በወቅቱ የጣሊያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሉዊጂ ዲ ማዮ፤ ጣሊያን ከኢትዮጵያ ጋር በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ ያላትን ግንኙነት አጠናክራ ለመቀጠል ፍላጎት እንዳላት አስታውቀዋል፡፡

በተለይም በኢኮኖሚ ዘርፉ ከአግሮ ኢንዱስትሪና የልማት ስራዎች ጋር በጋራ ለመስራት ጣሊያን ቁርጠኛ መሆኗን ገልጸው፤ ይህን የአገራቱን ግንኙነት ይበልጥ በማሳደግ ረገድ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ለኢትዮጵያ የቀረበው የብድር አቅርቦትም ጣሊያን የኢትዮጵያን የልማት ስራዎች ለመደገፍ ያላትን ፍላጎት እንደሚቀጥል ያሳየ ነው ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ያለውን የአግሮ ኢንዱስትሪ አምራችነት ለማሳደግ ያለመው የድብር ስምምነት በአራት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚመረቱ ምግቦችን ጥራትና ደረጃ ለማሻሻልም ይረዳል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ውስጥ ለሚገቡ አምራቾች፣ ለሰራተኞችና ተጠቃሚዎች አዲስ የቢዝነስ አማራጮችን ለመፍጠር የሚያግዝና የአግሮ ኢንዱስትሪዎችን ምርታማነት የሚያሻሽል መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በራሺያና ዩክሬን ጦርነት ምክንያት የዓለም የምግብ ግብዓት አቅርቦት ላይ ችግር እየተፈጠረ

ጣሊያን ከኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ፡- አዮብ ተፈራ

አቶ መሐመድ ሁሴን

# ተፈናቃዮችን በዘላቂነት ለማቋቋም በትኩረት እየሠራ መሆኑን የአፋር ክልል አስታወቀ

አብዱረዛቅ መሐመድ

ሰመራ፡- በሕወሓት የሽብር ቡድን ወረራ ምክንያት ንብረት የወደመባቸውና ከአካባቢያቸው የተፈናቀሉ ዜጎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመመለስና በዘላቂነት ለማቋቋም በትኩረት እየሠራ መሆኑን የአፋር ክልል አደጋ መከላከልና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ

ተፈናቃዮችን በዘላቂነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# «የግዥ ባህሪ ብቻ የነበረውን ተቋም ከስውጡ ወዲህ የማምረቻ ተቋም አድርገነዋል»

- አምባሳደር ምስጋናው አርጋ
የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ዋና ስራ አስፈጻሚ

አዲሱ ገረመው



አዲስ አበባ፡- የግዥ ባህሪ ብቻ ይዞ የነበረውን -የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ተቋም ከለውጡ ወዲህ የማምረቻ ተቋም አድርገነዋል ሲሉ የግሩፑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ገለጹ፡፡

የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አምባሳደር ምስጋናው አርጋ የተቋሙን የሥራ እንቅስቃሴ አስመልክተው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በቀድሞ ስሙ "ሜቴክ" ተብሎ ይጠራ የነበረውና ከለውጡ ወዲህ ስሙን የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ወደሚል ስያሜ የቀየረው ተቋም ቀድሞ የግዥ ተቋም ባህሪ ብቻ ይዞ ነበር፡፡ ከለውጡ ወዲህ ግን ሙሉ የማምረቻ ተቋም እየሆነ ይገኛል፡፡ በዚህም ምንም አይነት የግዢ ባህሪ እንዳይኖረው ተደርጓል፡፡

«የግዥ ባህሪ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

DERBA CEMENT



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን፡፡
ነገን ዛሬ እንሥራ





አርሾ
ሜዲካል ላቦራቶሪ ኃ.የተ.የግ.ማ
ARSHO MEDICAL LABORATORIES P.L.C
በትውልድ የታመነ!
አድራሻ - አራት ኪሎ፣
ከአራዳ ክፍለ ከተማ ሕንፃ ጀርባ፣
የ24 ሰዓት አገልግሎት
612
0114-16-70-89
0911-10-18-18

አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደበኛ ኮልሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

UNIC ETHIOPIA
ሕብረት ኢንሹራንስ አማ
THE UNITED INSURANCE COMPANY SC
Tomorrows Company Today'
ለሁሉም የመድን ፍላጎትዎ
ለህይወት ህጋዊ ግዴታዎ ለንብረት
+251 111 26 34 34
@united.insurance@unic-ethiopia.com
7469

# የትራፊክ ሕጉን በማሻሻል የሚስተዋሉ አደጋዎችን መቀነስ እንደሚገባ ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን የትራፊክ ሕግን በማሻሻል አሁን የሚስተዋሉ የትራፊክ አደጋዎችን መቀነስ እንደሚገባ ብሉምበርግ ኢንሼቲቪ አስታወቀ።

በትናንትናው እለት የመድህን ደሕንነትና መንገድ ፈንድ አገልግሎት በኢትዮጵያ የመንገድ ደሕንነት የሕግ ማዕቀፍ ሥራ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ አውደ ጥናት አካሂዷል።

በአውደ ጥናቱ ላይ ‹‹በኢትዮጵያ የመንገድ ደሕንነት የሕግ ማዕቀፎችን ማሻሻል›› በሚል ርዕስ ጽሑፍ ያቀረቡት የብሉምበርግ ኢንሼቲቪ የሕግ ማስከበር አስተባባሪ አቶ ቶሎሳ ገዳ እንደገለጹት፤ በሕግ ያልተሸፈኑ ጥፋቶችና ዝቅተኛ የሆነ ቅጣት ያላቸው ጥፋቶች አሉ፤ በጥቅሉ የትራፊክ ሕጉ በርካታ ክፍተቶች አሉበት ብለዋል። እንዲሁም አግባብነት ላለው ጥፋት አግባብነት ያለው ቅጣት ያልተቀመጠላቸው ጥፋቶች በርካታ በመሆናቸው አደጋዎች መበራከታቸውን ገልጸዋል።

ለሁሉም የትራፊክ አደጋ የጥፋት ደረጃ መቀመጥ አለበት ያሉት አቶ ቶሎሳ፤ በሰአት አንድ መቶ ኪሎ ሜትርና ሃምሳ ኪሎ ሜትር አሽከርክሮ አደጋ ያደረሰ



አሽከርካሪ እኩል መቀጣት የለባቸውም፤ ነገር ግን አሁን በኢትዮጵያ ያለው ሕግ ይህን ከግንዛቤ ያስገባ አይደለም። የትራፊክ ሕግን በመፈተሽና በማሻሻል ከሌሎች ሀገራት ልምድ በመውሰድ አደጋዎች መቀነስ ይገባል። በተለይ የቤልት አጠቃቀም፤ ከሞተር ሳይክል፣ ከፍጥነትና ከአልኮል አጠቃቀም አንጻር የተቀመጡት የሕግ አንቀጾች በጣም ክፍተት አለባቸው። በዚህም የተነሳ ከፍተኛ የሆነ የትራክ አደጋ እየተከሰተ በመሆኑ ጠንካራ ሕግ እንደሚስፈልግ ገልጸዋል።

ሌላው የትራፊክ አደጋ ችግር የሆነው የመንጃ ፈቃድ ቁጥጥር አለመኖሩ ነው ያሉት ጽሑፍ አቅራቢው፤ መንግሥት ራሱ የሰጠውን መንጃ ፈቃድ ሊቀጣጠር ይገባል፤ ከልተቆጣጠረ ከባድ ችግር ይፈጠራል። አንድ ሰው የወሰደውን መንጃ ፈቃ እንዴት ነው እየተገበረው ያለው የሚለውን በመከታተልና በመቆጣጠር የሚስተዋሉ አደጋዎችን መቀነስ እንደሚገባ ገልጸዋል።

በሌሎች ሀገራት መንጃ ፈቃድ በተለየ ሁኔታ ቁጥጥር ይደረግበታል፤ በኢትዮጵያ ይህ ነገር አይስተዋልም። በሕገወጥ መልኩ የሚወጡ መንጃ ፈቃዶች እየተበራከቱ ከፍተኛ የሆነ የትራፊክ አደጋዎች እያደረሱ ነው ብለዋል። መንጃ ፈቃድ በፌዴራልና በክልሎች ደረጃ የሚሰጥ በመሆኑ ወጥነት አለመኖሩን ገልጸዋል። በሌሎች ሀገራት በተደጋጋሚ በሚያጠፉና ከባድ ጥፋት በሚያደርሱ አሽርካሪዎች መንጃ ፈቃድን እስከ መንጠቅ የሚደርስ እርምጃ በመኖሩ የትራፊክ አደጋ ችግር እምብዛም አይስተዋልም ብለዋል።

በመድህን ደሕንነትና መንገድ ፈንድ አገልግሎት የመድሕን ኦፕሬሽን ዳይሬክተር አቶ አዲል አብዱላሂ በበኩላቸው የትራፊክ ሕጉ በርካታ ማነቆዎች አሉበት፤ ለማሻሻል የውይይት ስራዎች ተጀምረዋል። የሕጉ ማዕቀፎች ምን ይመስላሉ፣ አሰራሩና አፈጻጸሙስ የሚለውን ዳሶ በማጥራት ሕጉን ለማሻሻል እንደሚሰራ ገልጸዋል። በትራፊክ ሕጉ የአሰራር ሥርዓት ችግሮች እየተስተዋሉ ነው። አጠቃላይ ያሉ ችግሮችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመገምገምና ከሌሎች ሀገራት ተሞክሮችን በመውሰድ ለሕብረተሰቡ የሚጠቅም የሕግ ማዕቀፍ ይወጣል ብለዋል።



# በደቡብ ክልል በሰባት ዞኖች ላይ ተምች መከሰቱ ተገለጸ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ ክልል ሰባት ዞኖችና ሦስት ልዩ ወረዳዎች ውስጥ በ334 ሺህ 760 ሄክታር ማሳ ላይ አዲሱ መጤ ተምች መከሰቱን የደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ ገለጸ።

የደቡብ ክልል ግብርና ቢሮ የግብር የአዝዕርት ልማትና ጥበቃ ዳይሬክተር አቶ ወንድማገኘ ኃይለማሪያም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፣ በክልሉ በሚገኙት 7 ዞኖችና 3 ልዩ ወረዳዎች በ334 ሺህ 760 ሄክታር ማሳ ላይ አዲሱ መጤ ተምች ተከስቷል።

አዲሱ መጤ ተምች የተከሰተባቸው ሰባቱ ዞኖች ደቡብ ኦሞ፣ ጋሞ፣ ኮንሶ፣ ጎፋ፣ ካምባታ ጣምባሮ፣ ስልጤና ጌዴኦ እንደሆኑ የገለጹት አቶ ወንድማገኝ፣ ደራሼ፣ አሌና ባስኬቶ ደግሞ የተምች ወረርሽኙ የተከሰተባቸው ሶስቱ ልዩ ወረዳዎች መሆናቸውን ተናግረዋል።

በክልሉ በያዝነው የበልግ ወቅት በሰባት ዞኖች በአገዳ ሰብሎች ከተሸፈነው ማሳ 322 ሺህ 204 ሄክታር ላይ የተምች ወረርሽኝ ተከስቷል።

የተምች ወርርሽኙም በነፍሰ ወከፍ በ28 ሺህ 219 የአርሶ አደሮች ማሳ ላይ መከሰቱን የገለጹት አቶ ወንድማገኝ፣ በጾታ ስብጥርም 26 ሺህ 953 በወንድ እና ሶስት ሺህ 158 የሴት አርሶ አደሮች ማሳ ላይ ተከስቷል ብለዋል።

በመከላከል ሥራ ላይ 10 ሺህ 73 ሄክታር ማሳ ላይ የተባይ ቁጥጥር ስራው ተከናውኗል ሲሉ የተናገሩት አቶ ወንድማገኝ፣ በአራት ሺህ 556 ሄክታር ማሳ ላይ አራት ሺህ 556 ሊትር ፈሳሽ ፀረ-ተባይ ኬሚካል በመርጨት እንዲሁም በአምስት ሺህ 517 ሄክታር ላይ ደግሞ ማሕበረሰቡ ተባዩን በእጅ ለቅሞ በመግደል የመቆጣጠር ስራ ተሰርቷል ብለዋል።

እንደ አቶ ወንድማገኝ ገለጻ፣ በዘንድሮ በልግ ወቅት የዝናብ ሁኔታ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ያልተስተካከለ በመሆኑ በተለይም በደረቅ ቆላማ አካባቢዎች የተባዩ ክስተት ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ ነው።

አቶ ወንድማገኝ አክለውም፣ በቀጣይም የተባዩ ክስተት ሊቀጥል ስለሚችል ሁሉም አካባቢዎች የአሰሳና ቅኝት ሥራውን አጠናክሮ በመቀጠል የባህላዊ የመከላከል ዘዴን መሠረት በማድረግ የቁጥጥር ሥራውን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል ብለዋል።

# በአሲዳማ መሬት ላይ ኖራን ከተፈጥሮ ማዳበሪያ አሰባጥሮ በመጠቀም ምርታማነትን ለማሳደግ እየተሰራ ነው

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- በአሲዳማ መሬት ላይ የኖራ ዱቄትን ከተፈጥሮ ማዳበሪያዎች ጋር አሰባጥሮ በመጠቀም ምርታማነትን ማሳደግ እንደሚገባ ግብርና ሚኒስቴር ገለጸ።

ግብርና ሚኒስቴር የአፈር ለምነት ማሻሻያ ዳይሬክተር አቶ ተፈራ ሰለሞን እንደገለጹት፣ በአሲዳማ መሬት ላይ የኖራ ዱቄትን ከተፈጥሮ ማዳበሪያዎች ጋር አሰባጥሮ በመጠቀም ምርታማነትን ማሳደግ ይገባል።

በአገራችን በጠንካራ በአሲዳማነት የተጠቃ 3 ነጥብ 7 ሚሊዮን ሄክታር መኖሩን የገለጹት አቶ ተፈራ፣ ከዚህ ውስጥ አንድ ነጥብ 51 ሚሊዮን ሄክታር ብቻ ማከም ቢቻል በአገር አቀፍ ደረጃ 24 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ተጨማሪ ምርት ማግኘት ይቻላል ብለዋል።

በዚህም በደጋማ አካባቢዎች ብቻ ከሚመረቱ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ገብስና ባቄላ ምርት በዓመት 24 ነጥብ 5 ሚሊዮን ኩንታል ተጨማሪ ምርት ማግኘት እንደሚቻል ገልጸዋል።

እንደ አገር በገንዘብ ሲታሰብ በአንድ ጊዜ ብቻ የሚጨመረው ኖራ ለሶስት ዓመታት ተመሳሳይ የምርት ጭማሪ ሊያስገኝ የሚችል ነው ያሉ ሲሆን፣ በዓመት 30 ቢሊዮን ፣ በሶስት ዓመታት ደገሞ 91 ቢሊዮን ብር የተጣራ አገራዊ ገቢ የሚያስገኝ መሆኑን አመላክተዋል።

በአሲዳማ መሬት ላይ የኖራ ዱቄትን ከተፈጥሮ ማዳበሪያዎች ጋር አሰባጥሮ በመጠቀምም የእርሻ መሬቱን ለምነት ጠብቆ ለማቆየትና ለትውልድ አላቂ የሆነውን ሀብት ለምነቱን ጠብቆ ለማስተላለፍ እንደሚያስችልም አቶ ተፈራ ተናግረዋል።

የአፈር አሲዳማነትና ጨዋማነት መስፋፋትና በመሬቱ ውስጥ የሚገኝ የተፈጥሮ ቁስ አካል እየተመናመነ መምጣት እንደ አገር ምርታማነትን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ እንዲመጣ አድርጓል ያሉት አቶ ተፈራ፣ በዚህም የተነሳ በምግብ እህል ራስን ለመቻል እየተሳነን እንገኛለን ብለዋል።

አሲዳማ በሆነ መሬት ላይ ኖራን ከተፈጥሮ ማዳበሪያዎች ጋር አሰባጥሮ አርሶ አደሮች ቢጠቀሙ ያለኬሚካል ማዳበሪያ የሚፈለገውን ምርት በሂደት ማግኘት እንደሚቻል ሊታወቅ ይገባልም ብለዋል።



አሲዳማ መሬት በኖራ ሳይታከም ማዳበሪያ መጠቀም የማዳበሪያውን ውጤታማነት ከ 56 በመቶ በላይ የሚቀንስ ስለሆነ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። በመሆኑም አሲዳማ መሬትን ማከም ከማዳበሪያ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ተናግረዋል።

እንደ አገር የእርሻ መሬትን መንከባከብ የዳበረ ልምድ የለንም ያሉት አቶ ተፈራ፣ ማንኛውም በግብርና የሚተዳደረው አርሶ አደርም ሆነ ባለሀብት ከመሬት የሚገኘውን ምርትና ተረፈ ምርት አሟጦ በመውሰድ ወደ አፈሩ የመመለስ ልምድ ማዳበር ይገባዋል ብለዋል። በዚህም ከጊዜ ወደ ጊዜ የአፈሩ ጤንነትና ለምነት እንዲመጣ ማድረግ ያስችላል ብለዋል።

አቶ ተፈራ እንደገለጹት በአገራችን በብዛት የእርሻ መሬት ያለ ኬሚካል ማዳበሪያ ምንም ምርት የማይሰጥበት ደረጃ ላይ በመድረሱ ለከፋ የማዳበሪያ ጥገኝነት ብሎም የውጭ ተጽዕኖ እየተጋለጥን እንገኛለን።

የመሬት አፈር አላቂ ነው። ለቀጣይ ትውልድ ለምነቱ ተጠብቆ የምናወርሰው መሆኑን አውቀን ከወዲሁ ተገቢውን እንክብካቤ ልናደርግለት ይገባል ሲሉ አቶ ተፈራ መክረዋል።

የአሲዳማ አፈር ግብዓት የሆነውም የግብርና ኖራ ለአርሶ አደሩ ተደራሽ ለማድረግ የግል ሴክተሩ ተሳትፎ አስፈላጊ በመሆኑ የግብርና ኖራ ማምረት ላይ የተሰማሩ የሲሚንቶና የኖራ ፋብሪካዎች ግብዓቱን እያመረቱ ለአርሶ አደሩ ቢያቀርቡ ለምርትና ምርታማነት ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማበርከታቸውም ባሻገር ለስራ ዕድል ፈጠራም የማይናቅ ሚና እንደሚኖራቸውም ተናግረዋል።



# አቶ ደመቀ መኮንን ከጣሊያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር በሁለትዮሽ ጉዳዮች ላይ መከሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ከጣሊያኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሊዊጂ ዲ ማዮ ጋር በሁለትዮሽና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ዙሪያ ተወያዩ።

አቶ ደመቀ በዚህ ወቅት ከጣሊያኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር በሁለትዮሽ ግንኙነት፣ በቀጠናዊ ጉዳዮችና በዓለም አቀፍ ጉዳዮች ላይ ምክክር ማካሄዳቸውን ገልጸዋል።

የሁለቱ ሀገራት ግንኙነት ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ መሆኑን ጠቅሰው የጣሊያን መንግሥት ፥ በኢትዮጵያ የነበረው ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ሚዛናዊነት በማሳየቱ ምስጋና አቅርበዋል።

የሁለቱን ሀገራት የጋራ ጥቅም በሚያረጋግጥ መልኩ ፍሬያማ ውይይት ማድረጋቸውንም አቶ ደመቀ መኮንን ጠቁመዋል።

የጣሊያኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሉዊጂ ዲ ማዮ ለሁለት ቀናት ይፋዊ የስራ ጉብኝት አዲስ አበባ የገቡ ሲሆን ፥ በኢትዮጵያ የሚያደርጉትን ጉብኝት ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ኬንያ እንደሚያቀኑ የጣሊያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ጉብኝት ጣሊያን ከአፍሪካ አገራት ጋር ያላትን ትብብር ማጠናከር ዓላማ ያደረገ መሆኑንም ኢዜአ ዘግቧል።

ሚኒስትሩ ቀደም ብለው ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እንዲሁም ከኢጋድ ዋና ፀሃፊ ዶክተር ወርቅነህ ገበየሁ ጋር መወያየታቸው የሚታወስ ነው።

# ከግብርና ምርቶች ኤክስፖርት ከ2 ቢሊዮን በላይ ዶላር ገቢ መገኘቱን ሚኒስቴሩ አስታወቀ

- **ከ710 ቶን በላይ የግብርና ውጤት ጥራትና ደሕንነቱ ተረጋግጦ ወደ ውጭ ተልኳል**

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ከግብርና ምርቶች ኤክስፖርት 2 ነጥብ 2 ቢሊዮን ዶላር መገኘቱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

ባለፉት የበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት 710 ሺህ 364 ቶን የግብርና ምርቶችን ጤንነት፣ ጥራትና ደሕንነት ተረጋግጦ ወደ ውጭ ተልኳል።

የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ዑመር ሁሴን እንደገለጹት፤ በ2014 በጀት ዓመት በዘጠኝ ወራት ውስጥ የግብርና ምርቶችን የወጭ ምርት ግብይት ለማሳደግ ጥረት ሲደረግ መቆየቱን ገልጸዋል። ከግብርና ምርት ውጤቶች 2 ነጥ 2 ቢሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ገቢው ከአለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በ388 ሚሊዮን ዶላር ጭማሪ አሳይቷል ብለዋል።

የግብርና ምርት ኤክስፖርት በአጠቃላይ በሀገር ደረጃ ወደ ውጭ ተልኮ ከተገኘው 3 ነጥብ 29 ቢሊዮን ዶላር ገቢ 70 በመቶ ድርሻ መያዙንም ሚኒስትሩ አብራርተዋል።

ከግብርና ኤክስፖርት ከተገኙ ምርቶች ቡና ቀዳሚውን ቦታ እንደሚይዝ የገለጹት አቶ ዑመር፤ የቡና ምርት በዘጠኝ ወራት ውስጥ ወደ ውጭ ከተላኩት ምርቶች 45 በመቶ የሚሆነው ቡና እና 19 በመቶ የሚሆነው የአበባ ምርት ከፍተኛ ድርሻ እንደሚይዙ ጠቁመዋል።

በግብርና የወጪ ንግድ ላይ ከፍተኛ የፋይናንስ አቅርቦት ውስንነት አለ ያሉት ሚኒስትሩ በቀጣይ ችግሩን ለመፍታት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ይሠራል ብለዋል።

በተጨማሪም የግብርና ምርቶች ጥራትን ለማረጋገጥ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ አቶ ኡመር ተናግረዋል። የግብርና ምርት ኤክስፖርትን ለማሳደግ ጥራት ወሳኝ እንደሆነ የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ የግብርና ምርቶችን ጤንነት፣ ጥራትና ደሕንነት አረጋግጦ ወደ ውጭ ለመላክ የታቀደው 682 ሺህ ቶን ቢሆንም ከዕቅድ በላይ



710 ሺህ 364 ቶን የግብርና ምርት ምርመራ በማከናወን የምርቶችን ጤንነት፣ ጥራት እና ደሕንነት በማረጋገጥ ወደ ውጭ መላክ መቻሉን አብራርተዋል።

በተመሳሳይ ወደ ውጭ ለሚወጡ የዕፅዋት ምርቶች ከ12 ሺህ በላይ የደሕንነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መሰጠቱን ተናግረዋል።

ወደ ውጭ የሚቀርቡ የእንስሳት የሥጋ ምርቶች ጥራት የቅድመ እርድ እና ድሕረ ዕርድ ምርመራ ማከናወን መቻሉንም ሚኒስትሩ አስታውቀው፤ 1 ነጥብ 8 ሚሊዮን የዳልጋ ከብቶች ላይ የቅድመ ዕርድ ምርመራ መደረጉን እና 1 ነጥብ 6 ሚሊዮን እንስሳት ላይ የድህረ ዕርድ ምርመራ መደረጉን አቶ ዑመር ገልጸዋል።



# በክረምት ወራት 6 ነጥብ 8 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል

አዲስ አበባ፡- በአረንጓዴ አሻራ አራተኛ ዓመት መርሀግብር ማጠቃለያ በሆነው በተያዘው የክረምት ወር 6 ነጥብ 8 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል መታቀዱን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሀብት ልማትና እንክብካቤ ዳይሬክተር አቶ ተፈራ ታደሰ ከትናንት ወዲያ ለበሪሳ ጋዜጣ በሰጡት መግለጫ የአረንጓዴ አሻራ ሥራ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በዓይነትና በብዛት እየጨመረ መምጣቱን አውስተው፣ በ2011 ዓ.ም በ4 ነጥብ7 ቢሊዮን ችግኝ የተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር በዚህ ዓመት 6 ነጥብ 8 ቢሊዮን ችግኝ መድረሱን ገልጸዋል።

በ2012 እና በ2013 ዓ.ም በተከታታይ 5 ነጥብ 9 እና ስድስት ቢሊዮን ችግኞች በመርሀ ግብሩ መተከላቸውን አስታውቀዋል። በዚህ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር አራተኛ ዓመትና የመርሀ ግብሩ የመጀመሪያ ዙር ማጠቃለያም 6 ነጥብ 8 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶች እየተጠናቀቁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በእስካሁኑ ሂደትም የደንና የዛፍነት ጸባይ ያላቸው 47 በመቶ፣ ለምግብነትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውሉ ችግኞች ደግሞ 53 በመቶ መዘጋጀታቸውን ተናግረዋል።

ለዘንድሮ የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር ከትግራይ ክልል በስተቀር ሁሉም ክልሎች ዝግጅት ሲያደርጉ መቆየታቸውን የገለጹት አቶ ተፈራ፣ በአሁኑ ወቅትም የችግኝ ዝግጅት ተጠናቅቆ የመትከያ ቦታዎች መለየታቸውንና የመትከያ ጉድጓድ ቁፋሮ እየተከናወነ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

እስካሁንም በኦሮሚያ ፤ ደቡብ ሕዝቦች እና ደቡብ ምዕራብ ሕዝቦች ክልል 300 ሚሊዮን ችግኞች መተከላቸውን ተናግረዋል።

የአረንጓዴ አሻራ ሥራ በየዓመቱ አዲስ መሆኑና ያጋጠሙ ጉድለቶችን እየተስተካከሉ የሚፈጸም መሆኑን ገልጸው፣ የዘንድሮ መርሀግብርም ለምግብነት ለሚውሉ ችግኞች ልዩ ትኩረት መሰጠቱ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብሩን ልዩ ያደርገዋለ ብለዋል።

በባለፈው ዓመት ከተተከሉት ችግኞች መካከልም 80 በመቶ መጽደቃቸውን አስታውሰዋል።

በዘንድሮ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ላይም ሕብረተሰቡ እንደተለመደው ወጥቶ በችግኝ ተከላ መርሀ ግብሩ በመሳተፍ አረንጓዴ ኢትዮጵያን ለትውልድ ማስተላለፍ እንዳለበት ዳይሬክተሩ ጥሪ አቅርበዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ እንደ ኦሮሚያ ክልል ዘንድሮ 4 ነጥብ 6 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል መታቀዱን ከክልሉ ግብርና ቢሮ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድም የ2014 ዓ.ም አረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር የሚጀመርበት ጊዜ መቃረቡንና የመርሀ ግብሩን አራተኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የችግኝ መትከያ ጉድጓድ ዝግጅት በመላ አገሪቱ ሲከናወን መቆየቱን ሰሞኑን በማህበራዊ ሚዲያ ገጻቸው በኩል ይፋ ማድረጋቸው ይታወቃል።

# አማራ ባንክ በ70 ቅርጫፎቹ አገልግሎቱን በይፋ ይጀምራል

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ከአንድ ዓመት ከሶስት ወራት በላይ ምስረታ ላይ የቆየው አማራ ባንክ ሰኔ 11 በ70 የተሟሉ ቅርጫፎቹ አገልግሎቱን በይፋ ይጀምራል፡፡ ባንኩ ከስድስት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ስራውን የጀመረ ሲሆን እስካሁንም ከአራት ቢሊዮን ብር በላይ በስራ ላይ ማዋሉን አስታውቋል።

የአማራ ባንክ በትናንትናው እለት በጠራው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ የባንኩ የቦርድ ሊቀመንበር አቶ መላኩ ፈንታ እንደገለጹት ባንኩ ሰኔ 11 በ 70 የተሟሉ ቅርጫፎቹ ስራውን በይፋ የሚጀምር ሲሆን፤ እስከ ሰኔ ሰላሳ ስራ የሚጀምሩት ቅርንጫፎች ቁጥር ከ 100 በላይ እንደሚያሳድግም ጠቁመዋል።


ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሴ

አቶ መላኩ ፈንታ

በኢትዮጵያ ባለ አክሲዮኖች ብዛት ክብረ ወሰን መስበሩን ያመላከቱት አቶ መላኩ ባንኩ ከፍተኛ የባለ አክሲዮን ቁጥር ማብዛት ብቻም ሳይሆን በውጭም በአገር ውስጥም ያሉ ኢትዮጵያውያን መጠነ ሰፊ ተሳትፎ የተመሰረተ ባንክ ነው ብለዋል።

አቶ መላኩ ፋንታ ባንኩ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ ሀገራዊ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ የተከፈተ ባንክ ሲሆን በሀገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ አስተዋጽኦ ለማድረግ የተጀመረ ባንክ ነው ብለዋል።

የባንኩ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሄኖክ ከበደ በበኩላቸው እስከ ሰኔ 30 አጠቃላይ 100 ቅርጫፎች ስራ እንደሚጀምሩ ጠቅሰው በመከፈቻው ቀን ሰኔ 11 ላይ 70 ቅርጫፎች ስራ ይጀምራሉ ብለዋል።

አቶ ሄኖክ ባንኩ በተለያዩ የተግባቦት ሥርዓት የመጣ ሲሆን በዋነኝነትም "ከጎንዎ ማን አለ" የሚለው ማስታወቂያ እንደሚገኝበት በመግለፅ የሰራተኛ እና የስራ ቁሳቁስ ግብዓት የማሟላት ስራ መከናወኑን ገልጸዋል፡፡

አቶ ሄኖክ ባንኩ የሕዝብ ባንክ መሆኑን ያነሱ ሲሆን እስካሁን በብሄራዊ ባንክ ደንብ መሰረት የአክሲዮን ሽያጭ የማድረግ ስራዎች መከናወናቸውን አንስተው በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች አክሲዮኖች ተሸጠዋል ብለዋል።

ባንኩ የማሕበራዊ አገልግሎቱን ለመወጣት እንዲያስችለው ሰኔ 11 ቀን ከጠዋቱ 12 ሰአት እስከ ምሽት 3 ሰአት ድረስ የአንበሳ ባስ ተጠቃሚዎችን ወጪ መሸፈኑን አስታውቀዋል። ተጠቃሚዎችም በዕለቱም ያለምንም ክፍያ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ እንዲሁም በዕለቱ በሁሉም የክልል ዋና ከተሞች በተመረጡ ሆስፒታሎች ለሚወልዱ እናቶች በባንኩ ስም የእንኳን ደስ ያላችሁ ስጦታም ይበረከትላቸዋል ተብሏል፡፡

እስከ ሰኔ 11 ባሉት ቀኖችም ባንኩ የፓናል ውይይት፣ የደም ልገሳ እና ሌሎችም መርሀ ግብሮች እንደሚኖሩት አስታውቋል።

# ጣሊያን ከኢትዮጵያ...

ከገፅ 1 የዞረ

መሆኑን የጠቆሙት የጣሊያኑ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፤ ይህን ተጽዕኖ ለመቋቋም ጣሊያን ለምግብ አምራችና አቀነባባሪዎች ድጋፍ እያደረገች መሆኑ አስታውቀዋል።

ከኢትዮያ መንግሥት ጋር የተደረገው የብድር ስምምነትም ከልማት ስራዎች ድጋፍ ጋር ተያይዞ የቀረበ ነው። በኢትዮጵያም ያለው የምግብ አቅርቦትና የአግሮ ኢንዱስትሪዎች እንቅስቃሴ እንዲያድግ ጣሊያን ድጋፏን አጠናክራ ትቀጥላለች ብለዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አህመድ ሽዴ በበኩላቸው፤ ጣሊያን ለኢትዮጵያ የልማት ስራዎች እያደረገች ያለውን ድጋፍ አድንቀው፤ የብድር አቅርቦቱም የቡልቡላ፣ የቡሬ ፣ የይርጋለምና የበአከር የተቀናጁ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለማልማት እንደሚውል ገልጸዋል።

እንደ አቶ አህመድ ገለጻ፤ ኢትዮጵያና ጣሊያን ረጅም ዘመን ያስቆጠረና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የባህል ግንኙነት አላቸው። ጣሊያን ለኢትዮጵያ የምታደርጋቸው ድጋፎች በዋናነት በአግሮ ኢንዱስትሪ ልማት፣ በአገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር እንዲሁም በስደተኞች ጉዳይ ላይ ያተኮሩ ናቸው።

የጣሊያን መንግሥት በቀጣይም የኢትዮጵያን የልማት ስራዎች በተለይም የኢኮኖሚ ማሻሻያዎችንና የ10 የልማት ግቦችን መሰረት ያደረጉ ድጋፎችን እንደምታቀርብ ይታመናል፤ የኢትዮጵያ መንግሥትም የሁለቱ አገራት ግንኙነት ወደተሻለ ደረጃ እንዲሸጋገር ቁርጠኛ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በተመሳሳይ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከጣሊያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሉዊጂ ዲ ማዮ ጋር ትናንትና መወያየታቸው የሚታወስ ነው፡፡

በውይይታቸውም የአገራቱን ታሪካዊ የሁለትዮሽ ግንኙነት ማጠናከር በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ በተለይም ሁለቱ አገራት በባህል ዘርፍ ያላቸውን ግንኙነት ይበልጥ ለማሻሻልና በቀጣይ አዳዲስ ዘርፎች በትብብር መስራት በሚችሉባቸው ጉዳዮች ላይ መክረዋል።

በኢትዮጵያ የሁለት ቀናት ይፋዊ የስራ ጉብኝት ያደረጉት የጣሊያኑ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከኢትዮጵያ መንግሥት የተለያዩ የስራ ኃላፊዎች ጋር የሁለቱ አገራት ግንኙነት በሚጠናከርባቸው ጉዳዮች ላይ ውይይት አካሂደዋል።

# የፈረንሳይ መንግሥት በአማራ ክልል በጦርነቱ ለወደሙ የጤና ተቋማት ማቋቋሚያ የ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዩሮ ድጋፍ አደረገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ ፡- የፈረንሳይ መንግሥት በአማራ ክልል በጦርነቱ ለወደሙ የጤና ተቋማት መልሶ ማቋቋሚያ የሚውል የ 1 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዩሮ ድጋፍ አደረገ።

ፕሮጀክቱን ለመተግበር ጤና ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ የፈረንሳይ ኤምባሲ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመዋል።

ፕሮጀክቱ በቀዳሚነት የደሴ ሪፈራል ሆስፒታልን መልሶ የሚያቋቁም ሲሆን በሂደትም ሌሎች በጦርነቱ የተጎዱ የጤና ተቋማትን እንደሚደግፍ በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር ሬሚ ማሬሾ ገልጸዋል።

የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰም የተደረገው ድጋፍ ደሴ ሪፈራል ሆስፒታል የቀደመ አገልግሎቱን መስጠት የሚያስችለውን ቁመና እንዲገነባ ያደርገዋል ብለዋል።



አስፈላጊ የሚባሉ ጥገናዎችና ግብዓት የማሟላት ሥራም እንደሚከናወን ነው ያነሱት።

በተጨማሪም ሚኒስትሯ የፈረንሳይ መንግሥት ኮቪድን በመቆጣጠር ሂደት እገዛ ማድረጉን አንስተው አሁንም በጤናው ዘርፍ እያደረገ ላለው ድጋፍ አመስግነዋል።

# «የግዥ ባህሪ...

ከገፅ 1 የዞረ

ዋና ሥራ አስፈጻሚው እንዳሉት፤ ግሩፑ ለውጥ ካደረገ በኋላ የፋብሪካ ባህሪ ኖሮት ለኢኮኖሚው አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ በ"ፓዎር" ሴክተር፣ በግብርና ማሽነሪዎች፣ በኦቶሞቲቭ፣ በብረታ ብረት፣ በኤሌክትሮኒክስ፣ በኮንስትራክሽን ማሽነሪ፣ ማሽን በመገጣጠምና ለጥቃቅን ኢንዱስትሪዎች በማቅረብ ረገድ ሰፊ ሥራዎች እየተከናወነ ነው።

"ስንገጣጥም የሥራ እድል እንፈጥራለን። ቴክኖሎጂን መሠረት እናደርጋለን። የውጭ ምንዛሬን እናድናለን" ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ የግዥ ተቋም ባህሪ ብቻ ይዞ የነበረውን ሙሉ የማምረቻ ተቋም እያደረግን ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚው ተቋሙ በዋናነት እየሰራ ያለው ማምረት እንደሆነ ጠቁመው፤ በተለይ ኢንዱስትሪውን በኢኮኖሚው ውስጥ በማስገባት ለዕድገቱ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ በትኩረት እየሰራ እንዳለ ጠቅሰዋል። የለውጡ ዋና ማዕከል ኢንዱስትሪዎች ለኢኮኖሚው ደጋፊዎችና አምራች እንዲሆኑ ማድረግ እንደሆነ፤ በተለይ ከዚህ ቀደም ተገዝቶ ማስገባት ላይ ያተኩር የነበረውን ሙሉ በሙሉ እዚሁ የመገጣጠምና እሴት ጨምሮ ወደ ኢኮኖሚው የማስገባት ተግባር እየተከናወነ መሆኑንም ገልጸዋል። በሁሉም ዘርፍ ጥቅም ላይ ያልዋሉና ከዚህ በፊት የገቡ መሽነሪዎች ወደ ሥራ እንዲገቡ እየተደረገ ነውም ብለዋል።

ከለውጡ ማግስት የታለመለትን ግብ ለመምታት ጥሩ ጅምር እንዳለ ጠቁመው፤ ኢትዮ-ኢንጂነሪንግ ግሩፕ በአዲስ መልክ ከተቋቋመ በኋላ የሚጠበቅበትን ሚና በአግባቡ እየተወጣ እንዳለ ተናግረዋል። የሰው ሃይልን የማሰልጠንና የማብቃት፣ ያረጁ ፋብሪካዎችን የመለወጥ ሥራዎችን በማከናወን የአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ ድርሻ እንዲኖረው ታስቦ እንቅስቃሴ እየተደረገ እንዳለም ነው ያመላከቱት።

"ወደ ፊት የተለያዩ የግብርና ማሽነሪዎችን ባካተተ መልኩ ለመገጣጠም የሚያስችል ዝግጅቶች እያደረግን ነው። የጥገና ማእከላት በየክልሉ ለማቋቋም እቅድ ተይዟል። የአቅርቦት አቅምን ለማሳደግና ደንበኞች በተቋሙ ላይ እምነት ኖሯቸው አስተማማኝ አቅርቦት እንዲኖር እየሰራን ነው" ሲሉም ዋና ሥራ አስፈጻሚው አብራርተዋል።

በተለይ በግብርናው ዘርፍ የበጋ ስንዴን በማምረት ረገድ ክልሎች ሰፊ እንቅስቃሴ እያደረጉ እንዳሉና በአገር ደረጃ የተሳካ ውጤት መገኘቱን አስታውቀዋል።ግሩፑየግብርናማሽነሪዎችንበማገዝና ዘርፉን በመደገፍ ረገድ ውጤት ማስመዝገቡንም ተናግረዋል።

# ተፈናቃዮችን በዘላቂነት...

ከገፅ 1 የዞረ

ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

የጽሕፈት ቤቱ ዋና ኃላፊ አቶ መሐመድ ሁሴን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ሽብርተኛው የሕወሓት ቡድን በአፋር ክልል በፈጸመው ወረራ ምክንያት 645 ሺህ ዜጎች የተፈናቀሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ በክልሉ መንግሥትና በሌሎችም አካላት በተሠሩ ሥራዎች ሦስት መቶ ስምንት ሺህ ያህሉ ወደ ቀያቸው ተመልሰዋል።

እንደዋና ኃላፊው ገለጻ፤ በአሁኑ ሰዓት 336 ሺህ ተፈናቃዮች በክልሉ በሚገኙ 17 ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ይገኛሉ።

ተፈናቃዮችን ወደነበሩበት አካባቢ ለመመለስና በዘላቂነት ለማቋቋም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ዘርፈ-ብዙ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውም አብራርተዋል።

የሽብር ቡድኑ ወረራ በፈጸመባቸው አካባቢዎች የነበሩ የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሙሉ በሙሉ በመዘረፋቸውና በመውደማቸው ተቋማቱ ድጋፍ ተደርጎላቸው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በቅንጅት እየሠራ ነው ያሉት አቶ መሐመድ፤ ተፈናቃዮቹ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመመለስ ሌሎችም ቅድመ ዝግጅቶች እየተደረጉ ናቸው ብለዋል።

አካባቢዎቹ በሽብር ቡድኑ በወረራ የተያዙ ስለነበሩ አካባቢዎቹን ከጸጥታ ስጋት ነጻ ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር እንደሆነም ጠቁመዋል።

በሕወሓት የሽብር ቡድን ወረራ፣ በድርቅ፣ በጎርፍ አደጋ፣ በአንበጣ መንጋና በሌሎችም ምክንያቶች በክልሉ የምግብ ዋስትናቸው ጥያቄ ውስጥ የገባ ዜጎች ቁጥር አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን መድረሱንም አስታውቀዋል።

እርዳታ የማቅረቡና ተፈናቃዮችን በዘላቂነት የማቋቋም ሥራው በመንግሥት አቅም ብቻ የሚሸፈን ባለመሆኑ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ አቶ መሐመድ ጥሪ አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኮርፖሬሽኑን የመንደር ግንባታ እንደ ትምህርት ቤት!

የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን በሶስት ቢሊየን ብር ወጪ በ18 ወራት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ ገርጂ ያስገነባውን ዘመናዊ የመኖሪያ መንደር ባለፈው እሁድ አስመርቋል። ልብ በሉ መንደር ነው ተገንብቶ የተመረቀው። መንደሩ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መገንባቱም በምረቃ ስነስርአቱ ላይ ተገልጿል። መንደሩ የተገነባበት መንገድም ለዘርፉ በዓይነቱ ልዩ ተብሏል።

ግንባታው እንደ አገር በመኖሪያ ቤት ግንባታ ዘመኑን የዋጀ አዲስ የግንባታ ቴክኖሎጂ ይዞ የመጣ እንዲሁም የአገራችንን ባለሙያዎች ቴክኖሎጂና እውቀት ቀስመው በፍጥነት ተግባራዊ የማድረግ ብቃት ያሳዩበት መሆኑም ተጠቁሟል።

መንደሩ በሶስት ሄክታር ቦታ ላይ የተገነባና ባለአስር ወለል አስራ ስድስት ህንጻዎችን ያካተተ ነው። ቤቶቹም 510 ሲሆኑ፣ ከ150 እስከ 500 ካሬ ሜትር ስፋት አላቸው። ህንጻዎቹ በአልሙኒየም ፍሬምዎርክ ቴክኖሎጂ የተገነቡ መሆናቸውን ኮርፖሬሽኑ ገልጿል። እንደ መኪና ማቆሚያ፣ መዝናኛ፣ የልጆች መጫወቻና የመሳሰሉት ሌሎች የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ግንባታዎችንም ያካተተ ነው።

ግንባታው በብዙ መልኩ አድናቆት ሊቸረው የሚገባ ነው። ስር የሰደደ የመኖሪያ ቤት ችግር ባለባትና፣ በርካታ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታቸው እየተጓተተ እድሉ ለደረሳቸው ነዋሪዎች ሊተላለፉ ባልቻሉባት አዲስ አበባ ይህን አይነት የግንባታ ፍጥነት፣ ጥራት እና ወጪና ጊዜ ቆጣቢነት ለዚያውም በአንድ የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክት ላይ መመልከት በእርግጥም ትልቅ ስኬት ነው። ግንባታው ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ያካተቱ ግንባታዎች የተካሄዱበት መሆኑም እንደ የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታ ባሉ በሌሎች የመንግስት ግንባታዎች ያልታየ አዲስ ክስተት አንደመሆኑም ሊደነቅ ይገባዋል።

ለግንባታው የተለያዩ አቅርቦቶች ተሟልቶ መገኘት አስተዋጽኦው ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። ካለው ተሞክሮ አኳያ ሲታይ ይህ ግን ዋናው ጉዳይ ሊሆን አይችልም። የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ቁርጠኝነት፣ በግንባታው አዲስ የግንባታ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ መደረግ፣ ለመንደሩ ግንባታ በስኬት መጠናቀቅ ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

ግንባታን በተያዘለት ጊዜ ማጠናቀቅ እንደሚቻል በአንድነት ፓርክ፣ በወዳጅነት እና እንጦጦ ፓርኮች ግንባታ ላይ ማሳየት ተችሏል፤ የፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽንም በገርጂ የመኖሪያ መንደር ግንባታው ይህን ደግሞታል። ኮርፖሬሽኑ ባለፈው ዓመትም በመካኒሳ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ህንጻ ገንብቶ አሳይቷል። አሁን ደግሞ የገርጂን ፕሮጀክት በፍጥነት በማጠናቀቅ ያሳየው ስኬታማ አፈጻጸም ሌሎች ግንባታውን ከማድነቅ ባሻገር ተሞክሮ ቀስመው ግንባታቸውን ሊያሳልጡበት የሚገባ ነው።

እንደሚታወቀው አገራችን ጥሩ የግንባታ ተሞክሮ የላትም። ግንባታ ክፉኛ ሲጓተትባት የኖረችም ናት፤ አገሪቱ ዜጎች እንደ ዓይናቸው ብሌን የሚከታተሉት የህዳሴ ግድብ ግንባታ ጭምር ተጓትቶባት የነበረች አገር ናት። በአገሪቱ እንደ ሲሚንቶ ያሉ የግንባታ ግብአቶች አቅርቦት ችግር ቢታይም፣ አቅርቦቶቹ ተሟልተው በነበሩባቸው ወቅቶችም ግንባታን በተያዘለት ጊዜ መጨረስ የሚባል ነገር አልነበረም፤ ይህ ችግር አሁንም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ አልተቀረፈም።

ይህ ጉዳይ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታን ብቻ ወስዶ መመልከት ይቻላል። በአዲስ አበባ ከተማ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታቸው ባለመጠናቀቁ በርካታ የመኖሪያ ቤት እጣ የደረሳቸው ነዋሪዎች ለተደራራቢ ችግር እየተዳረጉ ናቸው። ቤቶቹ ግንባታቸው ስላልተጠናቀቀ ያልተላለፉላቸው በመሆኑ በአንድ በኩል ለኪራይ ቤት ወጪ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለባንክ ብድር እየከፈሉ ለከፍተኛ ችግር ተዳርገዋል። በእዚህ ላይ ባለው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ተሞክሮ መሰረት ቤቶቹ ሙሉ ለሙሉ ተጠናቀው የማይተላለፉ እንደመሆናቸው ቤቱን ሲረከቡ ደግሞ የማጠናቀቅ ስራ ይጠብቃቸዋል።

አገሪቱ በከተሞች ያለውን የመኖሪያ ቤቶች ፍላጎት ጥያቄን ለመመለስ ገና መንገዱን አልጀመረችም። የመኖሪያ ቤት ችግርን ለመፍታት ብዙ አማራጮችን ይዤያለው ያለን የከተማ እና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እየተጠናቀቀ ባለው 2014 በጀት አመት አንድም የመኖሪያ ቤት አለመገንባቱን ሰሞኑን የአስር ወራት የስራ አፈጻጸም ሪፖርቱን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረበበት ወቅት ማስታወቁን ለተከታተለ ደግሞ የመኖሪያ ቤት ጥያቄን የመመለሱ ስራ ገና ውሃው አለመሞቁን ነው መረዳት የሚችለው።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ባለበት እየረገጠ ያለበትም ሁኔታ ይህንኑ ችግር ያረጋግጣል። የከተማ አስተዳደሩ አዳዲስ ቤቶችን መገንባት መጀመሩ ቀርቶ ግንባታቸው ከተጀመረ ዓመታትን ያስቆጠሩትን ቤቶች አጠናቆ እጣ ለደረሳቸው ነዋሪዎቹ ለማስረከብ አለመቻሉ ሲታሰብ የመኖሪያ ቤት ግንባታው አሁንም ፈተና ውስጥ መሆኑን መረዳት ይቻላል። በሌሎች የመስሪያ ቤቶች፣ ህንጻዎች የመንገድና የመሳሰሉት ግንባታዎች የሚታየው መጓተት እና የጥራት ችግር መሰረታዊ ችግር ነው።

በዚህ ወቅት የኮርፖሬሽኑ የመንደር ግንባታ ተሞክሮ ትልቅ ልምድ ሊወሰድበት ይገባል። የኮርፖሬሽኑ ቤቶች እንዴት፣ በእዚህ ፍጥነትና ጥራት ወጪና ጊዜ ቆጣቢነት ሊገነቡ የቻሉት የሚለው በሚገባ ተጠንቶ በግንባታው ዘርፍ ለተሰማሩ አካላት ሁሉ ጥናቱ እንዲደርሳቸውና ተሞክሮውን እንዲጋሩት ማድረግ ያስፈልጋል።

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር እና የክልል ተመሳሳይ ተቋማት፣ እንዲሁም ሌሎች በግንባታው ዘርፍ ላይ የሚሰሩ የመንግስት ተቋማትና የግል ድርጅቶች እና ሌሎች የዘርፉ ተዋንያን ይህን ተሞክሮ መጋራት ይኖርባቸዋል።

ኮርፖሬሽኑ ያስመረቃቸው ቤቶች ከምረቃው በፊት በቅርቡ በመንግስት ባለስልጣናት ተጎብኝተዋል፤ የእነዚህ አካላት ግንባታውን መጎብኘት በተለይ ግንባታው የሚመለከታቸው አካላት ትምህርት እንዲወስዱ ያደርጋቸዋል። ጉብኝቱ ግን በእነሱ ብቻ መፈጸም አልነበረበትም። ሌሎች በግንባታው ዘርፍ ላይ የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትም ጉብኝት እንዲያደርጉ እድሉ ሊሰጣቸው በተገባ ነበር። እነዚህ አካላት ጉብኝቱን ማድረጋቸው ራሳቸውን እንዲመለከቱ ያደርጋቸዋልና አሁንም ጊዜው አይረፍድም።

እንዲህ አይነት ግንባታዎች አንድ ወይም ሁለት ብቻ ሆነው መቅረትም የለባቸውም፤ እንዲስፋፉ መደረግም ይኖርበታል፤ እንደ ምርምር ግኝት መታየት አለባቸው። ከዚህ የግንባታ አፈጻጸም በመነሳት የአገሪቱን የግንባታ መሰረታዊ ችግር ለመፍታት መንግስትም፣ የግሉ ዘርፍም ጥረት ሊያደርጉ ይገባል።

የህዝብ መሰረታዊ ችግር ሆኖ የቀጠለውን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት የኮርፖሬሽኑ አዲስ የግንባታ ቴክኖሎጂ፣ ቁርጠኝነት፣ ወጪና ጊዜ ቆጣቢነት ትልቅ ትምህርት ቤት መሆናቸው ግንዛቤ ተይዞበት መሰራት ይኖርበታል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር እና የችግሩ አሳሳቢ አሁናዊ ገጽታ

ገርማ መንግሥቴ

ከሁሉ አስቀድመን ለሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር ብያኔ እናስቀምጥ። ብያኔውንም በሁሉም ዘንድ ተቀባይነትን ባገኘውና እየተሰራበት ካለው እንውሰድ። ”ሕገ-ወጥ የገንዘብ ፍሰት በጠቅላላው የአንድን አገር ድንበር አቋርጦ ሕገ-ወጥ በሆኑ መንገዶች የተገኙ ገንዘቦች የሚዘዋወሩበት መንገድ ነው። በሙስና፣ በኮንትሮባንድ፣ በወንጀል ድርጊትና ቀረጥ ላለመክፈል የሚዛወር ሂሳብ ነው።” በዚሁ ወደ ጉዳያችን እንዝለቅ።

ከኢኮኖሚ ምሁራን ጀምሮ፣ የሚመለከታቸው ሁሉ እንደሚሉት፤ እኛም እንደምናውቀው ችግሩ አገሪቱን ለበጀት ጉድለት ከማጋለጡም በተጨማሪ መፍትሄ ሳይገኝለት በምጣኔ ሀብት እድገቷ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ማሳደሩ በሳይንስ የተረጋገጠ ነው። እውነቱ ይህ ሆና ሳለ፣ ቁጥጥሩ ከመቼውም ጊዜ በላይ ተጠናክሮ ቀጥሏል ተብሎ በሚነገርበት በዚህ ወቅት፣ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በሕገ ወጥ መንገዶች ገንዘብ የማሸሽ እና የማዛወር ሙከራ ተባብሶ መቀጠሉ የሚያስገርም ብቻ ሳይሆን የሚያሳዝንም፤ የሚያሳስብም ነው።

ምን ላይ እንደተደረሰ ባናውቅም፣ ኤፕሪል 8፣ 2021 ”ፖሊስ ባደረገው ምርመራ የተቀየረው የብር ኖት 174ሺህ 350 ብር፣ እንዲሁም 605ሺህ 550 ሐሰተኛ የኢትዮጵያ ብር በማዘጋጀት፣ በመገልገልና በማዘዋወር የተጠረጠሩ ግለሰቦች ላይ ሰባት መዝገቦችን በማደራጀት እያጣራ መሆኑን ገልጿል፡፡” የሚል ዜና ሰምተን ነበር።

”በተመሳሳይ በአዲስ አበባ 99ሺህ 852 የአሜሪካን ዶላር፣ 3ሺህ 555 ድራም፣ 210 ዩሮ፣ 2ሺህ 553 ሪያል፣ 5ሺህ 495 የሱዳን ገንዘብ፣ 1ሺህ 800 የኤርትራ ናቅፋ፣ 500 የደቡብ አፍሪካ ራንድ፣ እና ከ474ሺህ 500 ብር በላይ በተደረገ ብርበራ” መያዙን ሰምተናል።

ሲቀጥልም፣”ከ1ሚሊዮን 9መቶ ሺህ (1,900,000) በላይ ብር እንዲሁም የአሜሪካ ዶላርና የኤርትራ ናቅፋ በቁጥጥር ስር መያዙን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን” አስታወቀ (ኤፕሪል 14፣ 2020) በማለት ሲል አስታውቆናል”። የአገራችን እውነታ ይሄንን ይመስላል። ለትህትና ሲባል ”ይመስላል” አልን እንጂ ”ነው”።

ዜናዎቹ ቀጥለዋል፤ የቅርቦቹን ትተን የቀድሞዎቹን እንከታተል።

ቪኦኤ (28.02.2022) እንዳቀረበው፣ ህገወጥነቱ ከጥሬ ገንዘብም ባለፈ ኢትዮጵያ በጅቡቲ መስመር ብቻ አምስት አይነት የነዳጅ ምርቶችን የምታስገባ ሲሆን በየአመቱም 4ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ነዳጅ እንደምታስገባ ይታወቃል። ይህ በኢኮኖሚው ላይ የሚፈጥረው ጫና አንሶ ጭራሽ ”ኢትዮጵያ ለውስጥ ፍጆታ ከውጪ የምታስገባው የነዳጅ ምርት በሕገ ወጥ የንግድ ሰንሰለት ወደ ጎረቤት አገራት ለገበያ እየቀረበ በመሆኑ ይህ ሲደረግ ቢገኝ ነዳጁም፣ ያንን የጫነው ተሽከርካሪም በክልል የፀጥታ ኃይሎች እንዲወረስ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ አሳስበዋል።” የሚል ዜና ሰምተናል። (ደግነቱ ኢትዮጵያ ትልቅ አገር መሆኗ በጀ እንጂ ጅቡቲን የምታክል ብትሆን፣ እንደ ሙስናው ብዛት፣ ገና ድሮ የለችም ነበር።)

ይህ ብቻ አይደለም፣ ኢዜአ (ሀምሌ 27/2013) ”አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ከአዲስ አበባ እስከ ቶጎውጫሌ በዘረጋው ህገ-ወጥ የዶላርና የገንዘብ ዝውውር ኔትዎርክ፣ ሲጠቀምባቸው የነበሩ ሰነዶችና ገንዘብ ከነተጠርጣሪዎቹ መያዙን የኢትዮጵያ ፌደራል ፖሊስ ገለፀ፡፡ [...] ዶላሩን ከአዲስ አበባ በጥቁር ገበያ እየሰበሰቡ መንግስትን እንዲዳከም ሲሰሩ የተደረሰባቸው መሆኑንም ተጠቁሟል፡፡

አሸባሪው ቡድን ቀድሞ በሰራው ኔትዎርክ አማካኝነት በንግድ ተቋማት የሚሰበሰቡትን ዶላሮች በህገ-ወጥ መንገድ ከአገር እንዲወጣ በማድረግ ለሽብር ቡድኑ ዋነኛ የፋይናንስ ምንጭ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡ [...] ፖሊስ ከወንጀል ድርጊቱ ጋር ቀጥተኛ ተሳትፎ አድርገዋል ያላቸውን 6 አለም አቀፍ የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶችና 11 ግለሰቦች ከ14 ባንኮች የተከፈቱና 10 ሚሊዮን 276ሺህ 496 ብር ከያዙ ከመቶ በላይ የባንክ የሂሳብ ደብተሮች ጋር በቁጥጥር ስር አውሎ ምርመራ መጀመሩን አስታውቋል፡፡

ጁንታው በአዲስ አበባ ህጋዊ አሰራርን ሽፋን በማድረግ መንግስት እንዲዳከምና ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ለሚያስገባቸው ጥሬ እቃዎች የዶላር እጥረት እንዲያጋጥመው እንዲሁም የኑሮ ውድነትን አባብሶ ህዝብ በመንግስት ላይ እንዲነሳ ለማድረግ የሞከረ መሆኑንም ፖሊስ ደርሼበታለሁ ብሏል፡፡ የሽብር ቡድኑ በአገር ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫና በመፍጠር የኑሮ ውድነት እንዲባባስ ማድረጉም ተናግሯል፡፡” (ከላይ ”በዚህ ከቀጠለች ...” ያልነው ያለ ምክንያት እንዳልሆነ ልብ ይባል ዘንድ እንጠይቃለን።)

ከላይኛው ዜና መረዳት እንደሚቻለው ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውሩ የሚያስከትለው ጣጣ በቀላሉ የሚታይ አይደለ። አገሪቱን የዶላር እጥረት እንዲያጋጥም፣ የአገሪቱ ኢኮኖሚ እንዲሽመደመድ፣ የኑሮ ውድነት እንዲባባስ ... ማድረግ ድረስ የዘለቀ አደጋን ያስከትላል።

**ከአህጉሪቱስ አኳያ?**

ወደ አፍሪካ አህጉር እስከዛሬ ድረስ በእርዳታ መልኩ ከተለገሰው ገንዘብ ጋር ሲነጻጸር ከአፍሪካ የሚወጣው ህገ-ወጥ ገንዘብ በእጥፍ ይበልጣል። እንዴት? እንደሚከተለው።

”የግሎባል ፋይናንሻል ኢንቴግሪቲ (Global Financial Integrity) የተባለ ድርጅትን የሚመሩት ሬመንድ ቤከር አንድ ሰው በህይወቱ ሊያየው ከሚገባ በላይ ከአፍሪካ ገንዘብ በህገ-ወጥ መልኩ ሲወጣ ተመልክቻለሁ፤ በጥናትም አስደግፌ አረጋግጫለሁ ሲሉ በካፒተል ሂል ለተሰበሰቡ ተሳታፊዎች ተናግረዋል።” በማለት ለአየር ያበቃው የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ነው።

ሬመንድ “በዚህ እክል እንደ አፍሪካ ክፉኛ የተጎዳ የአለም ክፍል የለም። በአለም ዙሪያ ከታዳጊ አገሮች የሚወጣው ህገ-ወጥ የገንዘብ ፍሰት በአመት 1ትሪሊየን ዶላር ይሆናል፣” ማለታቸውንም በዛው ቶን፤ ጊዜ እና ቦታ ላይ ሆኖ አሳውቆናል። ታዲያ የአፍሪካ ሕዝብ ቢራብ፣ ቢጠማ፣ ቢጎሳቆል ... ምን ይገርማል? (ይህ የጁላይ 2010 ጥናት ሲሆን፣ ዛሬ በ2022 ወንጀሉ የት ሊደርስ እንደሚችል ማንም ሊያሰላው የሚችለው ጉዳይ ነው።)

”ከ1970 እስከ 2008 ድረስ ለነበሩት 39 አመታት ከአፍሪካ በህገ-ወጥ መልኩ የወጣው ገንዘብ ወደ 850 ቢሊየን ዶላር ይገመታል። በእርግጥ ይሄ ተመን የማያካትታቸው አጠራጣሪ አሀዞች በመኖራቸው፤ ገንዘቡ ከተባለው ሊበልጥ” ይችላል። ”በዚህ ጥናት መሰረት ኢትዮጵያ ከ16 ቢሊየን ዶላር በላይ ገንዘብ የሸሸ ሲሆን ከአፍሪካ በ13ኛ ደረጃ ትገኛለች። ለንጽጽር ያህል ጎረቤት ኬንያ 7ቢሊየን ዶላር (22ኛ) ጅቡቲ 1ቢሊየን ዶላር (45ኛ) ኤርትራ 117ሚሊዮን ዶላር (51ኛ) ደረጃን ይዘዋል።” እየመረረንም ቢሆን ልንውጠው የሚገባን ”እውነት” ይሄ ነው።

”በአፍሪካ ከፍተኛ ገንዘብ በህገ-ወጥ መልኩ የሚወጣባት አገር ናይጀሪያ ስትሆን 241 ቢሊየን ዶላር፣ ግብጽ 131 ቢሊዮን፣ ደቡብ አፍሪካ 74 ቢሊየን ዶላር በመሆን ከ1-3 ያለውን” ደረጃ የሚይዙ ናቸው፤ ”ኢትዮጵያ ስንተኛ ወጣች?” ብሎ የሚጠይቅ ካለ፤ ”እንደ አያያዟ በቅርቡ 1ኛ ...” የሚል ምላሽን ሊያገኝ ይችላልና እዳው ገብስ እንዳልሆነ ሁሉም ሊገነዘበው ይገባል። ይህ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ የግለሰቦች፣ የጥቂት ቡድኖች ወዘተ ሳይሆን የህዝብ ጉዳይ ነውና ማንም ማንንም አይታገስም፤ አያልፍምም። በዚህ በኩል ያለው ህግ የማስከበር ስራ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ነው።

ያ ከመሆኑ በፊት ግን፣ ወንጀለኞችም ከወንጀላቸው እንዲቆጠቡ፤ ህብረተሰቡም ከፀጥታ ሀይሉ ጋር በመሆን ኃላፊነቱን እንዲወጣ፤ መንግስትም እንደ መንግሥትነቱ የህግ የበላይነትን እንምዲያስከብር ማሳሰቡ የዚህ ፅሁፍ አቢይ ጉዳይ ነው።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የኢትዮጵያ መዳኒ እድል የሀሳብ የበላይነት ብቻ ነው

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

በአገር ግንባታ ላይ የላቀ ዋጋ ካላቸው ጉዳዮች አንዱ የሀሳብ የበላይነት ነው። አብዛኞቹ የአለማችን ስልጡን አገራት ከኢኮኖሚ የበላይነት ባለፈ ሉዓላዊነታቸውን የገነቡት በዚህ የላቀ እውነታ ውስጥ በማለፍ ነው። አሁን ላለችውም ሆነ ነገ ለምትፈጠረው አገራችን የሃሳብ የበላይነትን የመስፈን ጉዳይ ወሳኝ እንደሆነ ይታመናል። በተለይ እንደ እኛ አገር በብሔርና በቋንቋ፣ በባህልና በወግ፣ በታሪክና በስልጣኔ ለተሳሰረ ማህበረሰብ የሚያስፈልገው እንዲህ አይነቱ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እሳቤ ነው።

አብዛኞቹ ችግሮቻችን ንትርክ ወለድ ናቸው። አብዛኞቹ ዝቅታዎቻችን ከበላጭ ሀሳብ ይልቅ ለእኔነት ሀሳብ እጅ የሰጡ ናቸው። በአጠቃላይ አሁን ላይ እየተሰቃየንባቸው ያሉ መከራዎቻችን ሁሉ ከላቀ ማህበራዊ እሳቤ እጥረት የመነጩ ስለመሆናቸው ተጠራጣሪ አለ ብዬ አላስብም። እስካሁን ድረስ እየጎዱን ያሉ ነገሮች ሁሉ እያወቅናቸው ልብ ያላልናቸው ነገሮች ናቸው።

አንድን ነገር ማወቅና መረዳት የተለያየ ነገር ነው። ብዙዎቻችን በትምህርት፣ በልምድ በተለያየ መንገድ ብዙ ነገር ልናውቅ እንችላለን የምናውቀውን ነገር የተረዳን ግን ጥቂቶች ነን። አሁን ላይ አገር እየፈረሰች ያለችው ብዙ በሚያውቁ ግን ደግሞ የሚያውቁትን ባልተረዱ ጥራዝ ነጠቆች ነው። ህዝባችን ሁሉ ነገር በድህነት ላይ ቁምጥና ሆኖበት ያለው ከአብራኩ በወጡ አዋቂ ነኝ ባይ አላስተዋዮች ነው። መረዳት ስቃይ ሆኖ አያውቅም። መረዳት አቅጣጫው ወደ መፍትሄ ነው።

እኛ ኢትዮጵያውን እያወቅናቸው ግን ደግሞ ባልተረዳናቸው ማህበራዊ ስቃይ ውስጥ ነን። ተረድተናቸው ግን ደግሞ መፍትሄ ባልሰጠናቸው ፖለቲካዊና ማህበራዊ ችግሮቻችን ውስጥ ነን። እኚህን ስቃዮቻችንን ከማወቅ አልፈን እስካልተረዳናቸው ድረስ ከእዬዬ ባለፈ ለመፍትሄ የሚሆን አቅም አናገኝም። እኚህን ችግሮቻችንን ከመረዳት አልፈን መፍትሄ እስካልሰጠናቸው ድረስ ከአበሳ አናመልጥም። መጀመሪያ ችግሮቻችንን እንረዳቸው። ከዛ በጠረጴዛ ዙሪያ እንቀመጥ። ስንቀመጥ ግን በምክክር በችግሮቻችን ላይ የበላይ እንድንሆን እንጂ ባለመስማማት ሌላ ችግር ለመፍጠር አይደለም።

ሰው ካሰበ፣ ሰው ከተፋቀረ፣ ሰው ከተነጋገረ የማይፈታው ችግር የለም። በፍጥረታት ታሪክ ውስጥ ከሰው ልጅ የሚበልጥ ችግር አልተፈጠረም። ችግሩ የእኛ ፍቅር ማጣት ነው። ችግሩ የእኛ ራስ ወዳድነት ነው። ችግሩ የእኛ ሁሉንም አለመግባባት በጦርነት ለመፍታት መሞከራችን ነው። ችግሩ የእኛ አለመነጋገር ነው። ችግሮቻችንን ከተረዳናቸው ከእኛ በታች ናቸው። ካልተረዳናቸው ደግሞ ከእኛ በላይ ሆነው እያሰቃዩን ይኖራሉ። ምስጢሩ የመረዳትና ተረድቶም በምክረ ሀሳብ መፍትሄ መስጠቱ ላይ ነው።

እኛ አገር ችግሮቹን በምክክር ያሸነፈ ፖለቲከኛ የለም። እኛ አገር ልዩነቱን በእርቅ የፈታ ቡድን የለም። ችግሮቻችንን ለፖለቲካ ትርፍ ነው የምንጠቀማቸው። እኛ አገር ችግሮቻችን ሌላ ችግር እንዲፈጥሩ እሽሩሩ ነው የምንላቸው። እኛ አገር ፖለቲከኞቻችን ስልጣን መያዝ የሚፈልጉት የማህበረሰቡን ችግር አጉልቶ በማውጣት ነው። ይሄን ድንቁር፤ አላዋቂነት ነው ።

የእኛ እውቀት ምን አይነት ነው? በእውቀታችን አገርና ህዝብ ከሚያስጨንቁት ውስጥ ነን ወይስ ያወቁትን በመረዳት ለመፍትሄ ከሚቆሙት ውስጥ? አገር ወዳድ የሆናችሁ ሁሉ ይሄን ጥያቄ በመመለስ ለአገራችሁ ብርሃን መሆን ይቻላችኋል። አንድን ነገር ለማወቅ ሳይሆን ለመረዳት ሆነን እንቅረበው። አንድን ነገር ስንረዳው መነሻ ምንጩን ብቻ ሳይሆን መድረቂያውንም እንደርስበታለን። መድረቂያውን ተረዳነው ማለት ለከበቡን ችግሮች መፍትሄ መስጠት እንችላለን ማለት ነው። ስለዚህም እንደ ዜጋ፣ እንደ መንግስት ችግሮቻችንን ከማወቅ አልፈን ልንረዳቸው ይገባል። መፍትሄ ያለው በመረዳት ውስጥ ነው።

አገር ማለት ምን ማለት እንደሆነች ብንረዳ ኖሮ ዛሬ ላይ ይሄን ሁሉ መከራ ባልፈጠርንባት ነበር። መረዳት ከማወቅ እጅግ ይበልጣል። ማወቅ እውቀት ሲሆን

> **ከስህተት ሁሉ ስህተት ያለ አላማ መኖር ነው። ያለአላማ መኖር የዚህ ዓለም የመጨረሻው ስህተት ነው። በሕይወት ጉዞ ውስጥ የምንደነቃቀፍባቸው እንቅፋቶች ሁሉ ከዚህ አላማ አልባ ማንነት ውስጥ የወጡ ናቸው። አላማ ራስን በግብረገብነት ውስጥ ማኖር ነው። አላማ ራስን ጠቃሚና አስፈላጊ አድርጎ ማቆም ነው። አላማ የአገር ፍቅር አንዱ ማሳያ ሆኖም ይቆጠራል**

መረዳት ግን ጥበብ ነው። ማወቅ መነሻ ሲሆን መረዳት ግን መድረሻ ነው። ሕይወታችንን በማወቅ ሳይሆን በመረዳት መኖር ያስፈልጋል። አገራችንን በማወቅ ሳይሆን በመረዳት ውስጥ እናፍቅር። መረዳት ሕይወትን ውብ የሚያደርግ የመጨረሻው የብስለት መለኪያ ነው። አንዳንድ ሰዎች ያወቃችኋቸው ሲመስላችሁ ሌላ ሰው ሆነው ግራ አጋብተዋችሁ አያውቁም? ይሄን ሁሉ ጊዜ አብሬው ሆኜ ላውቀው አልቻልኩም ያላችሁት ሰው የለም? አለ እንደምትሉኝ እርግጠኛ ነኝ። በቃ ማወቅ ማለት እንዲህ ነው...ውስን።

በመረዳት ጥበብ ውስጥ እንገንባ። መከራዎቻችንን በመረዳት ሀሳብ ውስጥ እናሸንፍ። እየፈረስንና እየባከንን ያለነው በትንሽ እውቀት ነው። ለአገርና ለህዝብ ስጋት ሆነን የቆምንው ወንዝ በማያሻግር እውቀት ነው። ለአገር ስጋት የማይሆን እውቀትና ጥበብ ያስፈልገናል። ለትውልድ ጠንቅ ያልሆነ ፖለቲካና ፖለቲከኛ ያስፈልገናል። አንዳንዶች ዋሽተው ያስታርቃሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ ዋሽተው ያጣላሉ። አሁናዊ የአገራችን መልክ እንዲህ አይነት ነው።

አገር የተሰራችው በእኔና በእናንተ እውቀትና መረዳት ነው። አገር የምትፈርሰውም በእኔና በእናንተ ፍቅር ማጣት ነው። ፍቅር ያስፈልገናል። ኢትዮጵያ ከምትባል ከአንድ እናት ማህጸን የበቀልን ጉራማይሌ መልኮች ነን። እንደ ርብቃ ልጆች መጋፋት ሳይሆን በመነጋገር መተቃቀፍ ነው የሚያዋጣን። በዚህ እውነት ውስጥ አዲስ ሰማይና ምድርን እንገንባ።

ጎጂ ነገሮችን ጨምሮ በሕይወታችን የምንፈልጋቸው ማናቸውም መልካም ነገሮች በእኛ አስተሳሰብ በእኛ ጭንቅላት የሚፈጠሩ ናቸው። ራሳችንን ለመልካም ነገር ካዘጋጀንው መልካም ነገርን መውረስ እንችላለን፣ በተመሳሳይ መንገድ ራሳችንን ለክፉ ነገር ካስገዛንው ያንኑ ስሜት ወደ ራሳችን እናመጣለን። የምናስበው ማንኛውም ነገር ነገ ላይ ሕይወታችን ሆኖ ወደ እኛ ይመጣል።

የነገ አለማችን ዛሬ በምንሆነው አሁናዊ ነገር የተዋቀረ ነው። ነገ ላይ ለአገርና ለወገን አስፈላጊዎች እንድንሆን በዛሬ ሕይወታችን ላይ ዋጋ ወዳላቸው ነገሮች መመልከት ይኖርብናል። አሁን ላይ አገር እየጎዱ ያሉት እኩይ ሀሳቦች ናቸው። “የእባብ ልጅ እባብ” እንደሚባለው እኩይ ሀሳቦች ደግሞ እኩይ ድርጊትን ነው የሚፈጥሩት። በበጎ ሀሳብ በጎውን እኛን መፍጠር እንችላለን።

በበጎው እኛ በኩል ደግሞ በጎዋን ኢትዮጵያ መፍጠር ይቻለናል። ስለዚህም በጎ እናስብ። ጎዳናችን የሚቀናው፣ ነጋችን ብሩህ የሚሆነው ዛሬ በምንሆነው ነገር ነው። የዛሬ የአገራችን ስቃይ የትላንት የፖለቲካ አስተሳሰብ ነው። ከከሰረ ሀሳብ ውስጥ የተዋጣለት ሕይወት አይገኝም። እንደአገር ሳንገዳገድ ወደፈለግንበት የምንሄደው ሩቅ የሚያደርስ ቀና እሳቤ በውስጣችን ሲኖር ነው።

ሀሳባችን እንድንገዛው እንዲገዛን አንፍቀድ ። የሀሳቡ ባሪያ.. የስሜቱ ሎሌ የሆነ ሰው መልካም መጨረሻ የለውም። ሀሳቦቻችን መንገድ ጠራጊዎቻችንም መንገድ ዘጊዎቻችንም ናቸው። ዛሬ ላይ በብዙ ደስታና ስኬት ከፍታ ላይ ወጥተው የምናያቸው እነሱ ትላንት ላይ መልካም ሀሳብ የነበራቸው ሰዎች ነበሩ።

ከስህተት ሁሉ ስህተት ያለ አላማ መኖር ነው። ያለአላማ መኖር የዚህ ዓለም የመጨረሻው ስህተት ነው። በሕይወት ጉዞ ውስጥ የምንደነቃቀፍባቸው እንቅፋቶች ሁሉ ከዚህ አላማ አልባ ማንነት ውስጥ የወጡ ናቸው። አላማ ራስን በግብረገብነት ውስጥ ማኖር ነው። አላማ ራስን ጠቃሚና አስፈላጊ አድርጎ ማቆም ነው። አላማ የአገር ፍቅር አንዱ ማሳያ ሆኖም ይቆጠራል።

ዛሬ ላይ አገር እየጎዱ ያሉት አላማ የሌላቸው ሰዎች ናቸው። ዛሬ ላይ በብሔር ሽፋን አገር እየበጠበጡ ያሉት አላማ የሌላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ናቸው። አገር አላማ ያለው ትውልድ፣ አላማ ያለው ዜጋ ትሻለች። ሕይወት ምን ያክል ውድና እጅግ ድንቅ ተፈጥሮ እንደሆነ የምንረዳው ከከንቱነት ርቀን ራሳችንን በአላማ ስናኖር ነው። ከትላንት እስከዛሬ አገራችን ላይ የደረሱ ጥፋቶች ሁሉ ከዚህ ማንነት ውስጥ የወጡ እንደሆኑ ምስክር አያሻንም። ያለአላማ መኖር እንስሳዊ ባህሪ ነው። የጭካኔና የስግብግብነት መገለጫ ነው። ስንፈጠርም በምክንያት ነበር። ምክንያታችን ደግሞ በታላቅ ዋጋ መኖር ነው። ታላቅ ዋጋ ያለው ደግሞ በአላማ ውስጥ ነው።

በርካታ ጥናቶች በአላማ መኖርን የትልቅ ነገር ማሳያ እንደሆነ ነው የሚናገሩት በተቃራኒው ደግሞ ሰው ያለ አላማና ያለ ራዕይ የሚኖር ከሆነ እንስሳዊ ባህሪን እየተላመደ በዙሪያው ላሉ ጨካኝና አስደንጋጭ መሆን ይጀምራል ይላሉ። ይሄ ብቻ አይደለም አላማ የሌለው ሰው ለመኖር የሚያጓጓ ነገር ስለሌለው ሀሳቡ ሁሉ ጎጂና አውዳሚ በመሆኑ ለሀገር ስጋት ፈጣሪ ነው በማለት ያክላሉ፡፡

አላማ ያለው ሰው ስህተት አይሰራም ስህተት ቢሰራ እንኳን ለመታረምና ለመስተካከል ራሱን ያዘጋጀ ነው። አላማ በማወቅ ተጀምሮ በመረዳት የሚጠናቀቅ ነው። በትንሽ እውቀት ውስጥ ትልቅ አላማ የለም። ትልቅ አላማ ያለው በትልቅ እውቀትና በትልቅ መረዳት ውስጥ ነው። ራሳችሁን ትልቅ በጣም ትልቅ እጅግ በጣም ትልቅ አድርጋችሁ ፍጠሩ። የሕይወትን ትርጉም ከምትረዱበት ቁም ነገር አንዱ ለራሳችሁ ክብርና ዋጋ በመስጠት በምትኖሩት ዛሬ ነው።

ዛሬ ላይ እኔና እናንተ በምንሆነው ነገር ነው አገራችን የምትፈጠረው። የአገራችን ፈጣሪ እኔና እናንተ ነን። ጠንካራ አገር ለመፍጠር በአላማ የተቃኘ ጠንካራ ሀሳብ ያስፈልገናል። እኛ ማለት የነገ ሀገራችን ፈጣሪዎች ነን። እኛ ማለት የነገ አለማችን መሀንዲሶች ነን፡ ለምንገነባው ብሩህ ነገ ጥሩ ግንበኛ መሆን ይጠበቅብናል። በባህሪና በስነ ምግባር በአላማም የታነጸ ጥሩ ዜጋ ሊወጣን ይገባል።

ዛሬ ላይ አገራችን ኢትዮጵያ ከምንም በላይ የሀሳብ የበላይነት የምትሻበት ጊዜ ላይ ነን። ልዩነትን የሚያጠብቅ የላቀ ሀሳብ ከእያንዳንዳችን ያስፈልጋል። በመከነ ሀሳብ የመከነች አገር ለመፍጠር በፍሬከርስኪ የሚንቀሳቀሱ ሞልተዋል። በሀሳባቸው ዘቅጠው አገር ለማዝቀጥ ታጥቀው የተነሱ የእንግዴ ልጆች እዛም እዚም አሉ። እኚህን ግለሰቦች በሀሳብ ማሸነፍ ይኖርብናል።

እኛ የአገራችን የነገ እጣ ፈንታ ወሳኞች ነን። እኛ የአገራችን የማዕዘን ድንጋዮች ነን። አላማ ባነገበ.. በላቀ ሀሳብ እናሸንፍ። ከእኛ ውጭ በእኛ ላይ ሀይል ያለው ማንም የለም። አላማ ካለን በሰከነና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ማሸነፍ እንችላለን። ከመጠላላት ውጭ ያለውን ዓለም በምክንያታዊነት መቃኘት ያስፈልጋል። ብዙዎቻችን መብቶቻችንን ለማስከበር ከፍቅር ይልቅ ጥላቻን፣ ከመነጋገር ይልቅ ሀይልን የምናስቀድም ነን።

ይሄ አይነቱ አካሄድ ለሀገራችን ሲጠቅም አላየንም። ይልቅ በእወቀትና በሰለጠነ መንገድ ለችግሮቻችሁ መፍትሄ በመስጠት ከሌሎች የተሻልን እንደሆንን ማሳየት ይኖርብናል። ጦርና ጎራዴ አውዳሚ ናቸው። ጥላቻና ሀይል በወንድማማቾች መካከል ትርፍ የላቸውም። ትርፋችን ያለው በሀሳባችን ውስጥ ነው። ትርፋችን ያለው በአንድነታችን ውስጥ ነው።

እስካሁን ትርፍ ያለው እየመሰለን በማይጠቅሙን ነገሮች እየከሰርን ኖረናል። እኛም ሳንጠቀም አገርም ሳንጠቅም ስር በሰደደ ድህነት ስንማቅቅ ኖረናል። የእስካሁኑ አገራዊ ገመናችን በእኛው ተለያይቶ መቆም የተፈጠረ እንጂ በምንም የመጣ አይደለም። የሚሰሩ እጆች፣ የሚያስቡ ጭንቅላቶች፣ ለውጥ የናፈቀው መቶ ሀያ ሚሊዮን ዜጋ እያለን ለጥሩ ነገር እድል ሳናገኝ በድህነት ማቀናል። ለዚች ድሀ አገር ተጠያቂዎች እኛ ነን።

ለዚህ ድሀ ህዝብ ሀላፊነትን የምንወስደው እኛ ነን። ሌሎችን ማድመጥ ራስን ከማድመጥ የሚመነጭ ነው። ከአፍራሽ አስተሳሰብ ወጥተን ወደ ሰለጠነ ዘመናዊ እይታ መሸጋገር ይኖርብናል። ማሸነፍን በመሳሪያና በጉልበት ሳይሆን በሀሳብ የበላይነት እንቀበለው። በልዩነት ውስጥ መግባባትን፣ ባለመስማማት ውስጥ መስማማትን ባህል እናድርግ። የምንታገለው ለአንድ አገርና ህዝብ እስከሆነ ድረስ የሚያቀያይመንና ቂም የሚያያይዘን ምንም የለም።

በአገር ስም የሚነግዱ ብዙ እድርባዮች እንዳሉ አውቃለሁ። በአገር ስም ራሳቸውን ለመጥቀም የሚታገሉ ስለመኖራቸው እኔም እናንተም ምስክሮች ነን። አብዛኛው አለመስማማታችንም ከዚህ የመነጨ ነው። አገር የሚለውጡ ትልልቅ ሀሳቦችን እየጣልን በትንሽ ሀሳቦች ላይ ጊዜአችንን የምናጠፋው ለዚህ ነው። አላማችን አንድ አገርና ህዝብ ቢሆን ኖሮ መስማማት አያቅተንም ነበር ።

አላማውን አገር ያደረገ ዜጋ ሰላምን እንጂ ጦርነትን አያውቅም። አላማውን ህዝብ ያደረገ ትውልድ ለጋር ጥቅም በጋራ ይተጋል እንጂ መለያየትን እንደ ትልቅ አላማ ይዞ አይንቀሳቀስም። እኛ ለዚች አገር እንደ ጌዲዮን በጽናት እንቁም። እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን ከሚል ኋላቀር አስተሳሰብ ወጥተን የብዙሃኑን ድምጽ የምንሰማበት ሰፊ ጆሮና ጽኑ ልብ እናዳብር። ከእኔነት ወጥተን በላቀ ህዝባዊ እሳቤ ከፊት የቆሙ መሪዎች እንሁን።

የግለሰብ ጉዳይ ከአገርና ህዝብ ጉዳይ አይበልጥም እያልን፤ እኔና እናንተ ከአገር አንበልጥም እያልን ለምን የሀሳብ ልዕልና በውስጣችን ጠፋ ? የሀሳብ ልዕልና ከራስ የሚጀምር ነው። ከአገርና ህዝብ የሚነሳ ነው። አገርና ህዝብን ከፊት ማስቀደም ነው። የአገርና የህዝብን ጉዳዮችን አንደኛ ማድረግ ነው።

አገሩን ያረዳ ህዝቡን ከድህነት መታደግ ያልቻለ እውቀትና ስልጣን በታሪክ ተወቃሽ ከመሆን ባለፈ የሚኖረው ጥቅም የለም። እኛ የአገራችን የነገ ዋስትናዎች ነን። ከእውቀት ወደ ጥልቅ እሳቤ፣ ከጥልቅ እሳቤም ወደ ጥልቅ መረዳት ልናሸጋግራት ይገባል።

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የህሊና መንገድ- የሲድቦል ቴክኖሎጂን በኢትዮጵያ

**ዳግም ከበደ**









የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 የስትራቴጂ ሰነድ የግብርና ዘርፍ 32 ነጥብ 8 በመቶ፣ አጠቃላይ አገራዊ ምርት 85 በመቶ የአገሪቱን የሰው ኃይል፣ እንዲሁም 90 በመቶ የውጭ ምንዛሬ ገቢ እንደሚያስገኝ ይጠቁማል። እንደ ስትራቴጂ ሰነዱ መረጃ ከሆነ፣ በአገሪቱ የተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎች ሲኖሩ፤ በዋናነት የሚጠቀሱት በግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ እና በአጋሮቹ የሚመሩት እንደሆኑ ይገልፃል።

የዲጂታል ግብርና ስርአት/ ሲስተም/ መገንባትና የግብርና ቴክኖሎጂ ስራ ፈጠራን መደገፍ እና ማበረታታት አስፈላጊ መሆኑን የሚጠቅሰው ይሄው ሰነድ፤ በመጀመሪያው በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠትና ለመተግበር የሚያስችል የተቀናጀ ስርዓት መፍጠር፤ ሁለተኛው ደግሞ ፈጠራን፣ የስራ እድል ማስገኘትን እና አካታችነትን የሚያበረታታ የግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች ለውጭ ገበያ በማቅረብ ብቃት አስፈላጊነት ላይ ያወሳል።

የሰለጠኑትና በኢኮኖሚ የበለፀጉት አገራት በተለይ የግብርና ዘርፋቸውን በቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ የምርምር ውጤት ማገዝ አመርቂ ውጤት ማስመዝገባቸው ይነገራል። ከዚያ ባለፈ ግለሰቦች እውቀትና የፈጠራ ክህሎታቸውን ተጠቅመው የሚያስተዋውቋቸው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና የፈጠራ ሃሳቦችም እንዲሁ ዘርፉን በእጅጉ ካዘመኑና ዓለም የደረሰበትን የእድገት ደረጃ ከበየኑት ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል እንደሆኑም ይገለፃል። በዚህ ምክንያት ለወጣቶችና ግለሰቦች የመፍጠር አቅም ልዩ ትኩረት ድጋፍ ይደረጋል።

የኢትዮጵያ መንግስትም "በዲጂታል ኢትዮጵያ 2025" የስትራቴጂ ዶክመንት ላይ የፈጠራና አዳዲስ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሃሳቦችን የሚያፈልቁ ባለሙያዎችን ማበረታታት አንዱ ግብ መሆኑን አስምሮበታል። በመሆኑም የአገሪቱን የግብርናና መሰል ተያያዥ ፖሊሲዎች ከዚህ አንፃር እንዲቃኙ በመስራት ላይ እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተለይ ከስራ እድል ፈጠራና ክህሎት ጋር በተገናኘ ወጣቶች ግብርናን ጨምሮ ልዩ ልዩ ዘርፎች ላይ ያላቸውን የፈጠራ ሃሳብ እንዲያሳድጉና ለማህበረሰቡ እንዲጠቅሙ ድጋፍ እንደሚደረግ እየወጡ ያሉት መረጃዎች ያመለክታሉ።

### የህሊና መንገድ

የዝግጅት ክፍላችን በዛሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ አምድም ከዚህ ከፈጠራና አዳዲስ ሃሳቦች ጋር በተያያዘ በግብርናው ዘርፍ ለየት ያለና ያልተለመደ የቴክኖሎጂ ሃሳብ ይዛ ብቅ ያለች ወጣት አዲስ ቴክኖሎጂ ሊያስተዋውቃችሁ ወድዷል። ይህቺ ወጣት በዓለማችን ላይ ከሚተገበሩ ሳይንሳዊና በቴክኖሎጂ የተደገፉ የግብርና ዘዴዎች መካከል "ሲድቦል ቴክኖሎጂ" አሊያም ዘርን ባልተለመደ መንገድ (ፍሬውን በኳስ አሊያም ልጆች በሚጫወቱበት ብይ መልክ በአፈርና በማዳበሪያ መልክ በማዘጋጀት) የመትከል ፅንሰ ሃሳብን በተግባር ላይ እያዋለች የምትገኝ ነች።

በሙያዋ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአርክቴክቸር (ንድፍ) ትምህርት (በተለይ በቤት ውስጥ ዲዛይን ላይ ትኩረቷን አድርጋ) የተከታተለች ሲሆን፣ የማህበረሰቡን የአኗኗር መንገድ የሚቀይሩ የቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ የፈጠራ ሃሳቦች ላይ በስፋት በመሳተፍ ትታወቃለች። በተለይ ዓለማቀፍ ንቅናቄዎችና በተፈጥሮና የስራ ፈጠራ ዙሪያ ላይ በሚሰሩ ተቋማት ላይ "young african leaders initiative alumni"፣ "The Women Entrepreneurship for Africa (WE4A)"፣ "Connect4Climate" በመሳተፍም ትታወቃለች፤ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ በምትሰራቸው ስራዎች የ"climate change for east africa earth champions" ነች። የዛሬ እንግዳችን ወጣት ህሊና ተክሉ "የሲድቦል ኢትዮጵያ" መስራችና ዋና ስራ አስፈፃሚ።

### ወደ ራዕይ የሚደረግ ጉዞ

ህሊና የከፍተኛ ትምህርቷን እስክትጀምር ድረስ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ቆይታዋ በፈጠራና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሃሳቦች ላይ እምብዛም ተሳትፎ አልነበራትም። ከዚያ ይልቅ ትማርበት በነበረው ስኩል ኦፍ ቱሞሮው ትምህርት ቤት የድራማና ቲያትር ክለብ ውስጥ መሳተፍን ትመርጥ ነበር። ይሁንና የረጅም ጊዜ ፍላጎቷ ወደሆነው የአርክቴክቸር ትምህርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የህንፃ ኮሌጅ ስትቀላቀል አዳዲስ ሃሳቦችና የፈጠራ ስራ ላይ ያተኮሩ ዝንባሌዎችን ታዳብር ጀመር። በተለይ "sustainable architecture" ማለትም የአየር ንብረት ተፅእኖን የሚቀንሱና በትንሽ ወጪ ለበርካታ ዜጎች መኖሪያ ቤት መገንባት የሚያስችሉ ሃሳቦች ትኩረቷን ይስቡት ጀመር። በተለይ ከሶስተኛ እስከ አምስተኛ ዓመት ተማሪ በነበረችበት ወቅት ከጭቃ፣ ከኮንቴይነር፣ ከአሸዋና ከቀርከሃ በቀላሉ የመኖሪያ ቤት ለመስራት በሚደረጉ አዳዲስ ሃሳቦች ላይ ተሳታፊ ትሆን ጀመር። ይህ ተሳትፎዋ ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥን በሚገቱ ሃሳቦች ላይ ይበልጥ እንድትሳብና በዚያ ዙሪያ ላይ እንድትሰራ መንገዱን ጠረገላት።

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመርቃ እንደወጣች የአየር ንብረት ችግርን የሚቀርፉ ሃሳቦችን ለማመንጨትና አዳዲስ የፈጠራ ቴክኖሎጂ ስራዎች ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት ያድርባታል፤ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስልጠናዎችን ትሳተፍ ነበር። በዋናነትም ከ"Young African Leaders Initiative (YALI)" የአየር ንብረት ተፅእኖን ለመቀነስ በሚደረጉ ሃሳቦች ላይ ስልጠና በመውሰድ የእውቀት አድማሷን አስፍታ ሰርተፍኬት መውሰድ ቻለች።

ወዲያው "climate change Africa" የሚል ኩባንያ አቋቋመች። በዚያም ኤክስፖዎችን ከማዘጋጀት ባለፈ በመላ ኢትዮጵያ በመዞር ኢትዮጵያውያን በጉዳዩ ላይ የእውቀት ሽግግር በማድረግ የአየር ንብረት ለውጥን የሚቋቋሙ የፈጠራና የቴክኖሎጂ ሃሳቦችን እንዲደገፉ እድሉን በማመቻቸት ልዩ ልዩ ስራዎችን ታከናውን ጀመር። በመሃል ግን በውጪ አገር ከሚኖር የምታውቀው ሰው በምትመካከርበት ወቅት በኢትየጵያ ውስጥ አዲስ ስለሆነና የአየር ንብረት ተፅእኖን ከመቀየር ባለፈ ለአርሶ አደሩ፣ ለመንግስትም ሆነ በግብርናውና ደን ልማት ላይ ለሚሰሩ ሁሉ ቀላልና ለአሰራር ምቹ የሆነ የዘር አዘገጃጀትና አተካከል ቴክኖሎጂን የማስተዋወቅ ውጥን (ሃሳብ) ተከሰተላት። ይሄ ሃሳብ ግብርና ላይ ያተኮረ ሲሆን "ሲድቦል ኢትዮጵያ" ኩባንያ ቴክኖሎጂን እንድትመሰርት ያስቻላት ነበር።

### "ሲድቦል" ምንድን ነው?

"ሲድ ቦል ምንም አይነት ኬሚካል ሳይገባበት የዶሮ ኩስን እንደ ማዳበሪያ በመጠቀም የሚዘጋጅ አነስተኛ ክብደት ያለው በአፈር ዘሩን እንደ ኳስ በማድቦልቦል የሚዘጋጅ ነው" የምትለው የሲድ ቦል ኢትዮጵያ መስራችና ዋና ስራ አስፈፃሚ ህሊና፤ ዋናው አላማ ችግኝ ማፍላት አሊያም ረጅም ጊዜ የሚወስደውን የዘር ማፍላት ሂደት ለማስቀረት ያለመ ቴክኖሎጂ እንደሆነ ትናገራለች። በተለይ ለአረንጓዴ ልማት የሚውለውን ችግኝ አፍልቶ እስከ መትከል ያለውን ሂደት ለማድረስ ጊዜ፣ ቦታና ሌሎች ረጅም ሂደቶች እንዳሉት በመግለፅም "ሲድቦል" ይህንን የሚያስቀር እንደሆነ ትገልፃለች።

እንደ ህሊና ገለፃ፤ የሲድቦል ቴክኖሎጂ ብዙ ሂደቶችን የሚያስቀር ነው። በተለይ በችግኝ ተከላ ወቅት የሚጠይቀውን ቁፋሮ፣ የመትከል ሂደት እንዲሁም በሰው ሃይል ሊደረስባቸው የማይችሉ ተራራማና የሸለቆ ቦታዎችን በደን በቀላሉ ለመሸፈን በድሮንና በአውሮፕላን ተጠቅሞ ለመዝራት የሚያስችል ነው።

በአፈርና ማዳበሪያ ተጠቅሎ በኳስ መልክ የተዘጋጀው ዘር አሊያም "ሲድቦል" በማብቀል ሂደቱ ከመሬቱ በላይ የሚቀመጥ ሲሆን የሚሸፈንም አይደለም። አጠቃላይ ክብደቱ 2ነጥብ2 ግራም ሲሆን ማንኛውም ዘር ያለው ችግኝም ሆነ አትክልት በቀላሉ ቴክኖሎጂ እንደሚዘጋጅ ትናገራለች። ከዚህ ቀደም ሰፊ ሽፋን የሚይዘው ከአየር ላይ ዘርን የመዝራት ሃሳብ በብዙ ምልኩ አስቸጋሪ እንደሚሆን ገልፃ በተለይ 50 በመቶ ብቻ የሚሆነው መሬት ላይ እንደሚደርስ ቀሪው በአእዋፋት እና በንፋስ እንደሚወሰድ ትናገራለች። ሲድቦል ቴክኖሎጂ ግን ክብደት ባለው አፈርና ማዳበሪያ የሚጠቀለል በመሆኑና ወፎችም ሆኑ ማናቸውም እንስሳት በቀላሉ ሊያገኙት ስለማይችሉ ብክነት እንደሌለውና በልዩ ሁኔታ ተመራጭ እንደሚያደርገው ታነሳለች።

### ሲድቦል ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት

ህሊና ላለፉት አራት ዓመታት በቴክኖሎጂው ላይ ከማጥናቷም ባሻገር የሲድቦል ፅንሰ ሃሳብን በኢትዮጵያ ለማስፋፋት ጥረት እያደረገች ነው። ፍቃድ አውጥታና ለተወሰኑ ሰዎች የስራ እድል ከፍታ በርካታ ዘሮችን በሲድቦል መልክ በማዘጋጀት ገበያ ላይ በውስን መልኩም ቢሆን (በዞማ ሙዚም የሳርቤት ቅርንጫፍና በአንድነት ፓርክ ውስጥ በሚገኘው) እያቀረበች ትገኛለች። አሁን ደግሞ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ የግብርና ምርምር ቴክኖሎጂ ላይ ከሚሰሩ ተቋማት ጋር ለመስራት ጥረት እያደረገች ነው። በተለይ ይህ ቴክኖሎጂ ለአርሶ አደሮች መቅረብ ስላለበትና በሰፊው መተዋወቅ ስለሚኖርበት በዚያ ጉዳይ ከግብርና ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር አብራ ለመስራት ለመነጋገር ጥረት እያደረገች መሆኗን ትገልፃለች።

ዋና ስራ አስፈፃሚዋ "ኢትዮጵያውያን በምግብ ራሳችንን እንድንችል ብዙ ፀጋዎችና በረከቶች የታደልን ነን። ያንን ግን መመልከት አልቻልንም" ትላለች። ይህ እንዲቀር ወጣቶች የፈጠራና አዳዲስ ሃሳቦችን የማስተዋወቅ አቅማቸውን ተጠቅመው እውን ሊያደርጉት ይገባልም ትላለች። እሷም በአጭር ጊዜ ውስጥ ፕሮጀክቱ በመላው ኢትዮጵያ እንዲስፋፋና የአገሪቱን ኋላቀር የግብርና ስራ በቴክኖሎጂና በሳይንሳዊ መንገድ እንዲቀየር የበኩሏን ማበርከት እንደምትፈልግ ትናገራለች። ህሊና በአሁኑ ሰዓት የሲድቦል (የዘርኳስ) ዘዴን ለኢትዮጵያ የግብርና ዘዴ እንዲመች በማድረግና አዳዲስ የምርምር ስራዎችን በማከናወን በመላው አገሪቱ እንዲተዋወቅ በመስራት ላይ ትገኛለች።

የዘር ኳሶችን "ሲድቦል" በጥንት ግብፃውያን የዓባይ ወንዝ ከዓመታዊ የጎርፍ መጥለቅለቅ በኋላ በወንዙ ዳርቻዎች ላይ ባሉ ደለል የሚተኛበት ስፍራ ላይ ለመዝራት ይጠቀሙባቸው እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳናል። በእስያ እና በሌሎች አካባቢዎች በተለይም በደረቃማ አካባቢዎች ጥቅም ላይ መዋላቸውንም መረጃዎች ያመለክታሉ። በዋናነት ዘሮቹ ለመብቀል ምቹ ሁኔታ እስኪፈጠርላቸው ድረስ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና በቀላሉ እንዳይጎዱ ይጠብቃቸዋል። በ1700ዎቹ በካሮላይና የምዕራብ አፍሪካ ባሮች፣ በአፍሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለውን የዘር ኳስ ዘዴ በመጠቀም ሩዝ ያመርቱ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ። ይህም ዘርን ከአእዋፍ በመጠበቅ እና ማሳው በሚጥለቀለቅበት ጊዜ እንዳይንሳፈፍ በማድረግ ረገድ የሲድቦል ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው። አሁንም ምእራባውያንና የበለፀጉ አገራት በሲድቦል ቴክኖሎጂ ሰፊ ጥናትና ምርምሮችን በማድረግ እንዲሁም የተሻሻሉ ዘዴዎችን በማስተዋወቅ ይጠቀሙበታል።

> **የሲድቦል ቴክኖሎጂ ብዙ ሂደቶችን ያስቀራል። በተለይ በችግኝ ተከላ ወቅት የሚጠይቀውን ቁፋሮ፣ የመትከል ሂደት እንዲሁም በሰው ሃይል ሊደርስባቸው የማይችሉ ተራራማና የሸለቆ ቦታዎችን በቀላሉ በደን ለመሸፈን በድሮንና በአውሮፕላን ተጠቅሞ ለመዝራት የሚያስችል ነው።**

# ወቅታዊ ትንታኔ

## የዲጂታል መገበያያ ገንዘብ ሌላው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ እንዳይሆን

**አስቴር ኤልያስ**





በኢትዮጵያ እንደ ክሪፕቶከረንሲ፣ ቢትኮይንና የመሳሰሉት ዲጂታል መገበያያ ገንዘቦች ለግብይት ወይም ለክፍያ መጠቀም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ያልተሰጠው ድርጊት በመሆኑ ኅብረተሰቡ ከመሳተፍ እንዲቆጠብ ባንኩ አስጠንቅቋል። ኢትዮጵያውያን በዲጂታል መገበያያ ገንዘብ እንዳይጠቀሙ ባንኩ ማሳሰቡ አገሪቱ ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ራሷን እንደማላቀቅ የሚቆጠር መሆኑን ደግሞ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ተናግረዋል።

ቢትኮይንና የመሳሰሉት ዲጂታል መገበያያ ገንዘቦችን አስመልክቶ አዲስ ዘመን ያነጋገራቸው በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ በኢኮኖሚክስ ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ግርማ እንደሚሉት፤ ክሪፕቶከረንሲ በስሩ እንደቢትኮይን የመሳሰሉትን የሚይዝ ሲሆን፣ ስሙ ኪሪፕቶግራፊ እንደማለት ነው። ክሪፕቶግራፊ ደግሞ የኦንላይ ደህንነት ስርዓት ነው። አንድን ዳታ ክሪፕቶ ማድረግ ምስጢራዊነቱን ጠብቆ ለማቆየት የምንጠቀምበት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት ነው። ክሪፕቶግራፊ የሚባል ስርዓትን ተከትሎ የሚፈጠር ገንዘብ ነው።

መረጃዎችም እንደሚያመለክቱት፤ ቢትኮይኖችም ሆኑ ሌሎች ክሪፕቶከረንሲዎች የኢትንተርኔት ወይም የበይነ መረብ ላይ መገበያያ ናቸው። በቢትኮይን ግብይት ውስጥ ያሉት የተወሰኑ ኮዶችና የምስጢር ቁጥሮች ብቻ ናቸው እንጂ ምንም አይነት የሚጨበጥ ገንዘብ የለም። ቢትኮይን የተሰራው ማንነታቸው ላልታወቁ ግብይቶች እንደ ገለልተኛ ያልተማከለ ስርዓት ነው። በተጨማሪም ይህ ምንዛሬ ባለቤቶች የሉትም። ምናልባትም፣ የመንግስት አካላትም ሆኑ ትላልቅ ኮርፖሬሽኖች በመረጋጋት ላይ ተጽዕኖ ማሳደር አይችሉም።

ረዳት ፕሮፌሰሩ፣ ገንዘብ አንድ ዋናው ባህሪው ደህንነቱ ወይም ምስጢራዊነቱን ለመጠበቅ እያንዳንዱ ኖት ላይ የየራሱ የሆነ ቁጥር ይደረግበታል ይላሉ። ይህን ቁጥር ባንኩ የሚያውቀው ሲሆን፣ ከዚህ ባለፈ ደግሞ በምሲጢራዊ ህትመት ውስጥ ያለፉ የማይታዩ ቁጥሮችም ይኖሩታል። ይህ ስምምነት ነውና ገንዘብ ተብሎ ሰው እንዲገበያይበት ስለሚደረግ አንዱ ባህሪው ተቀባይ መኖሩ ነው።

ወደክሪፕቶከረንሲ ስንመጣ ደግሞ ማዕከላዊ ባንክም ስለሌለው በዛ ስርዓት ውስጥ ላሉ ሰዎች ተዓማኒነቱን ለመጨመር የሚሰጥ ማስተማመኛ አለ። ያ ማስተማመኛ ‹ማይኒግ› በሚባል ቴክኖሎጂ ስርዓት ውስጥ የሚያልፍ ነው። በዓለም ላይ እንዲመነጩ የተደረጉ ቢትኮይኖች እስከ 2019 እኤአ 17 ሚሊዮን ነበር። ቢትኮይኑን እንዲመነጭ ያደረጉት በከፍተኛ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተጠቅመው ነው።

ረዳት ፕሮፌሰሩ፣ ገንዘብ ማተም ሲባል የሚታተመው ወረቀት ነው፤ የሚጠይቀው መስማማትን ብቻ ነው፤ ስለሆነም መንግስት የቱንም ያህል ማተም ይችላል። ክሪፕቶከረንሲ ላይ ግን እንደርሱ አይደለም፤ የኮምፒዩተር ስርዓት ነው። እዛ ደረጃ ላይ ለመድረስ ደግሞ ብዙ ሂደት ስላለው ዝም ብሎ እንደወረቀቱ ብር የሚታተም አይደለም፤ አንዱም ተመራጭ ያደረገው ልክ የወርቅ ያህል የሚያልፈው መንገድ ፈታኝ በመሆኑ ነው ይላሉ። ከዚህም የተነሳ በጣም ጥረትን የሚጠይቅ ነው። ስለዚህም ክሪፕቶከረንሲ፤ ሳይንቲስቶች፣ የሒሳብ ቀመር አዋቂዎች፣ የሶፍትዌር ኢንጂነሮች በከፍተኛ የዘመኑ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የሚፈጥሩት እንደሆነ ነው የተናገሩት።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ቢትኮይንን የፈጠረው ሰው ማንነት በግልጽ አይታወቅም። የሚጠራበት ስም የሐሰት ስም እንደሆነ ይነገራል። በእርግጥ የፈጠረው ግለሰብ አሊያም በቡድን ሊሆን እንደሚችልም ይገመታል። ቢትኮይንን ፈጠረ የተባለው ሰው እንዲኖሩ የፈቀደው እስከ 21 ሚሊዮን ቢትኮይኖችን ነበር። ማይኒንግ በሚባል ሂደት ውስጥ የተፈጠረው ቢትኮይን፣ የተፈቀደው 21 ሚሊዮን ቢሆንም እስከ እኤአ 2019 ድረስ 17 ሚሊዮን ቢትኮይን ተሸጧል። ለምሳሌ የኢትዮጵያ መንግስት ባለ ሁለት መቶ ብር ይህን ያህል፣ ባለመቶ ደግሞ ይህን ያህል ነው ያተምኩት ሊል ይችላል፤ ልክ እንደዛ ሁሉ 21 ሚሊዮን ቢትኮይኖች መታተም አለባቸው ተብሎ ተወስኖ ከ21 ሚሊዮኑ 17 ሚሊዮኑ ሊሸጥ ችሏል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት የቢትኮይን ፍላጎት ደግሞ ቀንሷል። ምክንያቱም ለምሳሌ የክሪፕቶከረንሲ የዋጋቸው ባህሪ በጣም ተለዋዋጭ ነው። አንዴ እኤአ በ2018/19 ገደማ አንድ ቢትኮይን አስር ሺ የአሜሪካ ዶላር ነበር። በዓመቱ ደግሞ በሶስት እጥፍ ቀንሶ ወደ 3 ሺ 500 ዶላር ገደማ ወርዷል። ተለዋዋጭነቱ ከፍተኛ በመሆኑ ፍላጎቱ በጣም እየቀነሰ መጣ። ዋጋውን የሚጨምረውና የሚቀንሰው በዛ የገንዘብ ስርዓት ውስጥ ያሉ ሰዎች ፍላጎት በመሆኑ ነው። አንድ ቢትኮይንን ውድ የሚያደርገው ለማመንጨት የሚወስደው ጊዜ ነው። ክሪፕቶከረንሲ ተለዋዋጭ የሚሆንበት ምክንያት በጅምር ላይ ያለ ኢንቨስትመንት በመሆኑ ነው። ራሱ የንግድ ስርዓቱ በየቦታው ባሉ ወኪሎች ፍላጎት የሚካሄድ ስለሆነ የተገደበ ጣራ የለውም።

ገንዘብ ማለት መተማመን ማለት እንደመሆኑ ቢትኮይን ላይ እምነት እንዲኖር በዳታ ዝውውር ወይም ኮድ ሲሰተም ነው ማምጣት የፈለጉት። ኩባንያዎች ደግሞ የሚፈልጉት ዋስትናን ነው። ምክንያቱም አንድ ኩባንያ ገንዘቡን እንደሚፈልገው አይነት ከዶላር ወደ የን ወይም ከየን ወደ ብር መቀየር ግድ ሊለው ይችላል። ከዚህም የተነሳ ኩባንያዎች ወዲህና ወዲህ ማለት ትርፉ ድካም ነው ብለው ስለሚያስቡ ወደቢትኮይን መግባት አማራጭ ነው ብለው ይወስዳሉ። ለዛም ነው ቢትኮይንን የፈጠሩት።

አሜሪካ ውስጥ ማይክሮሶፍትን ጨምሮ 14 የሚሆኑ ትልልቅ ኩባንያዎች ናቸው ተብሎ የሚታሰቡት። ከእነዚህ ኩባንያዎች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪም ያለ አበዳሪም ሆነ ወይም በባንክ ስርዓት ውስጥ ያለ ወይም እቃ የሚገዛ አሊያም ደግሞ ግብዓት የሚያቀርብ ሁሉ ተያይዟል ተብሎ የሚነገረው። ክሪፕቶከረንሲ በስሩ ብዙ ጉዳዮችን የያዘ ነው። የኮምፒዩተር ሶፍትዌሮች ኢንጂነሮች፣ በፋይናንስ ስርዓት ውስጥ ያሉ አካላት አሉ። በመሃል ደግሞ ስርዓቱን የሚመሩ ደላሎች አሉ።

ታዲያ ይህ ዲጂታል መገበያያ ገንዘብ እኛ አገር ላይ እንዳይሰራ የተከለከለው ለምንድን ነው ሲባል በአገራችን ያለው ነባራዊ ሁኔታ፣ የፋይናንስ ዝውውሮችና ግኝቶች ሲመጡ የደህንነት ጉዳይ ነው የሚሆኑት። ገንዘብ ነውና ሰው ማግኘት የሚፈልገው ዋስትና አለ። እኛ ደሃ አገር ነን፤ ለምሳሌ አንድ ሰው አንድ ባንክ ላይ ያስቀመጠውን ገንዘብ መውሰድ ፈልጎ ቢከለከል መላ ህዝብ ገንዘቡን ከባንኩ ያወጣል። ባንኮች ላይ ተቀማጭ ገንዘብ አይኖርም ማለት ነው ይላሉ።

ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ እንደሚሉት፤ ሌላው ምሳሌ ኤቲኤምን (Automatic Teller Machine) በአገራችን ለማስተዋወቅ ምን ያህል ጊዜ ፈጅቶ እንደነበር ይታወቃል። በዚህ ደረጃ ያለን የፋይናንስ ስርዓት ክሪፕቶከረንሲ ሲመጣበት ሌላ ዱብ እዳ ነው የሚሆንበት። ሌላው ቀርቶ መንግስት የማይቆጣጠራቸው የገንዘብ ስርዓቶች ተብለው ቀርቶ መንግስት የሚያውቀውና የሚቆጣጠረው ላይ እንኳ ያለው ነገር ይታወቃል። ትልቁ ነገር ይህ ነው እንጂ ክሪፕቶከረንሲ ለሌብነት ይዳረጋል የሚባለው ነገር አንገብጋቢው ሆኖ ሳይሆን እሱ ለእኔ ሁለተኛው ምክንያት ነው።

በእርግጥ ፌክ ክሪፕቶከረንሲን መስራት እጅግ በጣም ከባድ ነው። ስለዚህ የውሸት ነገር ውስጥ እንገባለን የሚባለው ነገር ዋና ሆኖ አይደለም። ስለዚህ ዋናው ነገር ነባራዊ ሁኔታውን ያላገናዘበ፤ ማለትም አሁን ያለንበት የፋይናንስ እድገት ደረጃ ወቅቱ አይደለም የሚል እምነት አለኝ ይላሉ።

ሁለተኛው ደግሞ ቢሆን እንኳ ክሪፕቶ ከረንሲዎች በጣም ተለዋዋጭ ናቸው፤ ዛሬ አንድ ሺ ዶላር ሆኖ ነገ ሁለት መቶ ዶላር ሊሆን ይችላል። በነጋታው ደግሞ 50 ዶላር ሊሆን ይችላል። ስለዚህ በጣም ተለዋዋጭ ስለሆነ እሱን መቀበል የሚችል የሕዝብ ስነ ልቦና አለ ወይ የሚል ጥያቄ የሚያጭር ነው። በውጭ አገር ያሉ አካላት ከዚህ የተነሳ ራሳቸውን እስከማጥፋት ደርሰዋል። ምክንያቱም በልጽገናል በሚሉ አገሮች ራሱ ተለዋዋጭነቱ ከፍ ያለ ተጽዕኖ አድርሷል።

ወደእኛ አገር ሲመጣ ደግሞ ያለችንን ሀብት ሙሉ በሙሉ ወደእዛ አሻገርን እንዲህ አይነት ተለዋዋጭ ባህሪ የሚያሳየን ከሆነ ይህን ቀውስ ሊሸከም የሚችል የስነ ልቦና ጽናት ይኖረናል ወይ የሚያሰኝ ነው። ስለዚህ የዚህ አይነት አደጋዎች ስላሉ አይመከርም ሲሉ ተናግረዋል።

ለእኛ አገር ነባራዊ ሁኔታ የማይመከርበት ሌላው ነገር የፋይናንስ ቁጥጥር ስርዓቱ እንኳን በቢትኮይን እየተመራ በማዕከላዊ ባንክ እንኳ እየተመራ ለገንዘብ ማጭበርበር እየተጋለጠ ነው። በአሁን ወቅት እንኳ ዶላር እየሸሸ ስለመሆኑ ማሰብ ያስፈልጋል። ስለዚህ በመደበኛ የገንዘብ ስርዓት ውስጥ እንዲህ አይነት ክፍተት ከተፈጠረ በማይታዩ ሰዎችና ስርዓት በሚተላለፍ ገንዘብ ደግሞ ምን ያህል አደጋ ሊደርስ እንደሚችል መገመት ይቻላል። እንዲህ ሆኖ እንኳ በእኛ አገር ውስጥ ክሪፕቶከረንሲን ለመግዛት ገንዘብ የሚያፈላልጉ አካላት እንዳሉ እየተነገረ ነው።

በእኛ አገር ውስጥ ጥቂት ባለሀብቶች በዚህ ጉዳይ የተቸገሩ አሉ፤ ንብረታቸው ብዙ አገሮች ላይ ያለ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች አሉ። ለምሳሌ ቢትኮይን የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ምን ያህል ሊሸከም ይችላል ቢባል ዓለም አቀፍ ኢንቬስተሮቻችን እንዳሉበት መጠን ነው። ዓለም አቀፍ ደረጃ የደረሱ ኢትዮጵያውያን ኢንቨስተሮች ካሉ ቢትኮይንን የሚፈልጉት እነዚሁ ሰዎች ናቸው እንጂ ተራው ህዝብ አይደለም። ምክንያቱም ዓለም አቀፍ ላኪዎችና አስመጪዎች በግብይቶቻቸው መሃል የሚያጋጥማቸው ስለሆነ ነው። እነዚህ ሰዎች በቁጥር ጥቂቶች ቢሆኑም በኢኮኖሚ ደግሞ ተጽዕኖ ፈጣሪ ናቸው። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች በዓለም አቀፍ የገንዘብ ዝውውር ስርዓት ውስጥ ይቸገራሉ። ያንን ፈተና ለማለፍ ሲሉ ቢትኮይኖችን ገዝተው ዓለም አቀፍ የገንዘብ ዝውውሩን ለማለፍ ይፈልጋሉ።

በዓለም ላይ ካሉ 190 ያህል አገራት መካከል በአሁኑ ጊዜ 113 አገራት ቢትኮይንን ይጠቀሙበታል። ስለዚህም በርካታ አገራት አጽድቀውታል ማለት ይቻላል። በእርግጥ የመገበያያ ስርዓትነቱ ጥያቄ ውስጥ የሚገባ አይደለም። እኛ ደግሞ ሌሎች አገራት የሚጠቀሙበትን የገንዘብ ዝውውር ማሳለጫ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በአብዛኛው እየተጠቀምንበት አይደለም።

ከዚህ ሌላ ደግሞ የቢትኮይን የገንዘብ ስርዓቱ የውጭ ምንዛሬ ሽሽትን እንዲያውም ያቀለዋል እንጂ እንዲቆም አያደርገውም። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ሁለት በመቶ አጠቃላይ አመታዊ ገቢዋን ከልማቱ የምታጣው በውጭ ምንዛሬ ገንዘብ ሽሽት ነው፤ በተለይ ይህ የሚታጣው በሚላኩና በሚገቡ እቃዎች አማካይነት ነው። በአሁኑ ሰዓት ጥንቃቄ እንደሚያስፈልገው እንደ አገሪቱ የመከላከያ ኃይል እኩል ለፋይናንስ ስርዓቱም ጥንቃቄ ማድረጉ ተገቢና አስፈላጊም ጭምር ነው።

ረዳት ፕሮፌሰሩ፣ በአሁን ሰዓት ኢትዮጵያ እየተጠቀመችበት ያለው የዶላር ስርዓትን ነው ይላሉ። በዚህ ስርዓት ውስጥ ያለው ስምምነት ነው። ብዙ አገሮች ዶላርን ዓለም አቀፍ መገበያያ ስላደረጉት ከዚህም የተነሳ ዶላር ዓለም አቀፍ ገንዘብ ሆኗል። ለምሳሌ የዶላር ባለቤት አሜሪካ ናት፤ ብሔራዊ ባንኳ ያትማል። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገራት ደግሞ ዶላርን ለማግኘት አፈር ከድሜ ይበላሉ። ስለዚህ ለዓለም አቀፍ የገንዘብ ብዝበዛ መጋለጥ ይሆናል።

ምናልባት የምናገረው ሐሳብ ከዓለም የኢኮኖሚ ስርዓት ጋር ሊቃረን ይችላል፤ ምክንያቱ እነርሱ የዓለም የኢኮኖሚ ስርዓትንና ንግድን ያሳያል ይላሉ። ነገር ግን እኔ ከኢኮኖሚው በላይ የደህንነት ጉዳይ ስለሚታየኝ ነው። በእርግጥ የዓለም ኢኮኖሚ አንድ የመገበያያ ገንዘብ ቢኖርለት ምቹ ይሆናል። ነገር ግን ፍትሃዊ የሆነ የንግድ ስርዓት በሌለበት ዓለም ላይ እንዲህ አይነት የገንዘብ ዝውውር ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም። ስለዚህ ቢትኮይን የሚባለው ተጨማሪ የገንዘብ ዝውውር ያውም ማንነቱ በማይታወቅ አካል እየተዘወረ ስለሆነ ተጨማሪ ስጋት ነውና ለእኛ አደጋ ነው የሚሆነው። ወደፊት ጊዜ ብሎም ቴክኖሎጂ የሚፈታው ነገር ነው።

በአሁን ሰዓት ቢትኮይን ትልቅ አስደንጋጭ ክስተት ነው። ምክንያቱም ክሪፕቶከረንሲን በአሁን ሰዓት ለመቆጣጠር አስቸግሯቸዋል። እነርሱ ቴክኖሎጂያቸው የመጠቀ፤ የህግ ማዕቀፋቸውም ጠንካራ ሆኖ ባለበት ሁኔታ እንኳ እየተቸገሩ ነውና ልብ ማለቱ ይበጃል ባይ ነኝ።

ምናልባት አንዳንድ ኢንቨስተሮች ኢንቨስትመንታቸውን በሚያካሄዱበት አገር ላይ እየተጠቀሙ እንደሆነ እየታየ ነው። ይህም ለራሳቸው የሚመቻቸው ከመሆኑም በተጨማሪ በቀላሉ ገንዘብ ለማሸሽ እንዲያመቻቸውም ጭምር ነው። እኛ አገርም በቀላሉ ገንዘብ ለማሸሽ ነው በሚል ጥርጣሬው አለ። ስለዚህ የቀረው ይቅር ብለን ብሔራዊ ባንክ የወሰደው እርምጃ ተገቢነቱ ላይ ብናተኩር መልካም ነው።

ከምንም በላይ ኢኮኖሚክ ናሽናሊዝም ላይ እነ ራሽያ፣ ቻይና እና ኢራንን፤ ዓለም አቀፍ የሆነ የራሳቸው ባንክ ለማቋቋም እያጣሩ ባለበት በዚህ ጊዜ ይህንን ነገር መጠቀም ማለት አደጋ ውስጥ እንደመግባት ይቆጠራል። ይህን የእነርሱን ቢትኮይን መጠቀም ማለት ራስን ለውጭው አካል ለቅኝ ግዥነት እንደማመቻቸት ይቆጠራል። እኛ እነርሱ ያላቸውን የፋይናንስ ስርዓትና ቴክኖሎጂ እስካልታጠቅን ድረስ ያንን እንተግብር ብለን የምንነሳ ከሆነ ቅኝ ግዛትን በላያችን ላይ እንደማወጅ ነው የሚቆጠረው። ሌላው ቀርቶ ዶላር ራሱ እጥረት እንዲከሰትብን ምን ያህል እንደሚሰሩ እውን ነው። ከዛ ውጭ እንዲህ እንደቢትኮይን አይነት ቴክኖሎጂዎች ሲመጡ ዲዛይን የሚያደርጉት ለራሳቸው እንዲመች አድርገው ነው። ከኢኮኖሚም በላይ ደህንነታችንን በእጃቸው መዳፍ ውስጥ ለማድረግ ነው የሚጥሩት። እኛ ደግሞ የራሳችንን ቴክኖሎጂ ተጠቅመንና ሌሎች ላቅ ያሉ ነገሮች ኖረውን እንጂ እንዲሁ የምንቀላቀለው አይደለም። በእርግጥ አሁን ሊኖረን የሚገባ የፋይናንስ የድጂታል ስርዓቱም አለን ይላሉ።

የዩኤስ ብሔራዊ ደህንነት ኤጀንሲ መረጃ እንደሚያ ሳየው፤ እኤአ 2009 የመጀመሪያው ብሎክ እና የመጀመሪያዎቹ 50 ቢትኮይኖች ተፈጠሩ። የመጀመሪያው የቢትኮይን ግብይት የተከሰተው 2009 ሲሆን፣ የመጀመሪያውም የቢትኮይን ገንዘብ ልውውጥ የተደረገው በዚሁ ዓመት መሆኑ ይታወሳል።

ረዳት ፕሮፌሰሩ እንደሚሉት፤ የቢትኮይን አድራጊ ፈጣሪዎቹ ፈጠርነው የሚሉት ናቸው። ኢትዮጵያ ዶላርን እንኳ የግብርና ምርቷን እንዲሁም ማዕድኗን ሸጣ እንዴት እንደምታገኝ ይታወቃል። አሁን ደግሞ ተጨማሪ የሆነ ሌላ የገንዘብ ስርዓት ቢትኮይን የምንል ከሆነ ሌላ የእጅ አዙር የቅኝ ገዢን ቀንበር በራሳችን ጫንቃ ላይ እንደማስቀመጥ ይቆጠራል።

ማህበራዊ

# ሴቶች



ፎቶ፡- በሃዲስ አብርሃ

ወይዘሮ ደሚቱ እጀታ፤



አቶ ታሪኩ ታመነ፤



ወይዘሮ መብራቴ አሰፋ፤

## የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ

አስናቀ ፀጋዬ

‹‹ለአገር እድገትና ብልፅግና የሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎ ወሳኝ ነው›› ሲባል ብዙ ጊዜ ይደመጣል።በሚነገረው ልክ ግን አሁንም ድረስ በተሟላ መልኩ ሴቶችን ያሳተፈ የልማት እንቅስቃሴ ሲካሄድ አይታይም።የሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎም ሙሉ በሙሉ ተረጋግጧል ማለት አይቻለም።ይሁንና ከለውጡ በኋላ ሴቶችን በአመራርነት በማሳተፍ፣ በማህበራዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይም በንቃት እንዲሳተፉ በማድረግ ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴዎች እየታዩ መጥተዋል።

ሴቶች ሃብት ንብረት እንዲያፈሩ የተሰሩ ሥራዎችም ገና ብዙ ቢቀራቸውም በዚህ ለውጥ ጊዜ ጭላንጭሎች ታይተዋል።በተለይ ደግሞ ሴቶችን በከተሞች አካባቢ ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ ተጠቃሚ ማድረግ ለከተሞች እድገትም ሆነ ገፅታ ግንባታ አይነተኛ ሚና ይጫወታል።በመሆኑም በዚህ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራት ከፌደራልም ሆነ ከክልል መንግስታት ብዙ ይጠበቃል።

ይህንኑ ታሳቢ በማድረግም የሲዳማ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ርእሰ መስተዳደር ጽህፈት ቤት ከሐዋሳ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽህፈት ቤትና ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ጋር በመቀናጀት "የሴቶች ተጠቃሚነት በከተማ ገፅታ ግንባታ ወሳኝ ሚና አለው" በሚል መሪ ቃል ከሰሞኑ የንቅናቄ መድረክ በሀዋሳ ከተማ አካሂዷል።

የንቅናቄው ዋነኛ አላማም ሴቶች እንደከተማ ልማት በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይ እና በገፅታ ግንባታ ሥራ ላይ ያላቸውን ተጠቀሚነትና እኩልነት ለማረጋገጥ መሆኑ ተነግሯል። በዚህ የንቅናቄ መድረክ የክልል ከተሞች ሥራ ኃላፊዎች፣ ልዩ ልዩ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ አመራሮች፣ የእምነት ተቋማትና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተሳትፈው ለሴቶች ተጠቃሚነት ጠቃሚ ግብአቶች ተሰብስበዋል።

ወይዘሮ ደሚቱ እጀታ በሐዋሳ ከተማ አስተዳደር አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ፍላዴልፊያ ቀበሌ ታጋይ መንደር ነዋሪ ናቸው።በሚኖሩበት መንደርም የመንደር ተጠሪ ሲሆኑ፤ የመሰረታዊ ድርጅት አመራርም ናቸው።ከውሃ አጣጫቸው ጋርም ጋብቻ መስርተው አምስት ልጆችን አፍርተዋል።

በዚህ የለውጥ ሂደት ውስጥ ከሌሎች የመንደሩ ሴት ነዋሪዎች ጋር በመሆን ሥራዎችን እያከናወኑ እንዲሚገኙና በአሁኑ ጊዜ ሴቶች በብዙ መልኩ ተጠቃሚ መሆናቸውን ይገልፃሉ።ሴቶች ከወንዶች እኩል መስራት እንደሚችሉና እርሳቸውም ሆኑ እርሳቸው በሚኖሩበት መንደር ውስጥ ያሉ ሌሎች ሴቶች የተሰጣቸውን እድል ተጠቅመው በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይ በመሰማራት ውጤታማ እየሆኑ እንደሚገኙም ይናገራሉ።በአመራርነትም በመሳተፍ የመምራት ብቃት እንዳላቸው እያረጋገጡ መሆናቸውንም ይጠቅሳሉ።

እርሳቸው በሚኖሩበት መንደር የሴቶች የሶስትዮሽና የልማት መሰረታዊ ድርጅት ቡድን መኖሩንና ምሽት ላይ ለጥበቃ ከወንዶች እኩል እንደሚወጡ ያስረዳሉ።በመንደራቸው ሴቶች የከተማ ግብርናና የከብት እርባታ ዘርፍ ውስጥ በመሳተፍ ከወንዶች እኩል የራሳቸውን ሃብት እያፈሩ እንደሚገኙም ይጠቅሳሉ።በተመሳሳይ ሴቶች በአመራርና በውሳኔ ሰጪነት በመንደሩ ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ እንዳሉም ወይዘሮ ደሚቱ ይናገራሉ።

ሴት በቅድሚያ ቤቷንና ልጆቿን መምራት አለባት የሚሉት ወይዘሮ ደሚቱ፤ ቤቷንና ልጆቿን መምራት ከቻለች አካባቢዋን ከፍ ሲል ደግሞ አገሯን ለመምራት ምንም እንደማያዳግታት ያመለክታሉ።ነገር ግን አሁንም በተሳሳተ አመለካከት፣ በፍርሃትና በይሉንታ ምክንያት ወደኋላ የቀሩ ሴቶች መኖራቸውን አልሸሸጉም።

ሴቶች እነዚህን ጎታች ምክንያቶች ወደኋላ ትተው ወደፊት መውጣት እንዳለባቸው የሚመክሩት ወይዘሮ ደሚቱ፤ እርሳቸው በሚኖሩበት መንደርም በልማት ቡድን በኩል የጋራ ውይይት እንደሚካሄድና ሴቶች በቤታቸው ያለው ችግር ምን እንደሆነ እንዲያወሩና አጥሮ የያዛቸውን ነገር ሰብረው እንዲወጡ የማስተማር ሥራ እንደሚሰራ ያብራራሉ።

የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ምክትል ኃላፊ አቶ ታሪኩ ታመነ እንደሚናገሩት፤ የሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት መረጋገጥ ለከተማ ልማትና ለአገር ገፅታ ግንባታ ትልቅ ሚና አለው።በዚህም ሴቶች በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሐዋሳ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ በኩል ሰፊ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

ትልቁ ሀብት መሬት እንደመሆኑ መጠንና በተለይ ደግሞ በከተማ ከሚሰሩ ሥራዎችና ሴቶችም እንደቅሬታ ከሚያቀርቧቸው ችግሮች አንዱ የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ ነው።ከዚህ አንፃር ሴቶች መብቶቻውን ለመጠቀም፣ ከቤተሰብና ከውርስ ጋርም ያሉ ጉዳዮች ችግር እንዳይሆኑባቸው ለማድረግ ይሰራል።ይህም የሚሆነው ነገሮቹ የህግ ማዕቀፍ ሆነው እንዲቀጥሉ በማድረግ ነው።በተለይ በከተማ አስተዳደር የመሬት ምዝገባ ላይ ሴቶች በአግባቡ እኩል መብት እንዲኖራቸው ህጋዊነቱን ሊያረጋግጡ እንደሚገባም ይመክራሉ።

በዚህም በሐዋሳ ከተማ ባለፉት ዓመታት ከ12 ሺህ በላይ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሥራ ተሰርቷል።በዚህ ዓመት ደግሞ ከ5 ሺህ በላይ የሚሆን የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሥራ ተከናውኗል።በአንዳንድ የከተማዋ ክፍለ ከተሞችም ሥራው ሙሉ በሙሉ ተጠናቋል።በተለይ ደግሞ መናኸሪያ ክፍለ ከተማ ባህል አዳራሽ አካባቢ ሥራዎች ተጠናቀዋል።አሁን ደግሞ በምስራቅ፣ መሀልና አዲስ ከተማ ክፍለ ከተሞች ላይ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ሥራው በትኩረት እየተከናወኑ መሆኑንም ይናገራሉ።

የከተማው የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ትልቅ ፋይዳ ያለው በመሆኑና ለገቢ ሥራም ጭምር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ሴቶች ለዚህ ሥራ ድጋፍ እንዲያገኙና ይህም ሲረጋገጥ በቀጣይ ህጋዊ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ በእጃቸው እንዲኖራቸው ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሆነም ያስረዳሉ።

ሴቶች በኢኮኖሚ ተጠቃሚ በሚያደርጓቸው ሥራዎች ላይ፣ በፖለቲካ አመራርነት ላይም ራሳቸውን ማብቃት እንዳለባቸው፤ በተመሳሳይ በማህበራዊ ጉዳዮች ላይም ግምባር ቀደም ሆነው የራሳቸውን መብት ማስጠበቅና በተለይ ለከተማዋ ለሐዋሳ ውብና ፅዱ መሆን አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ በመሆናቸው በዚህ ረገድ ሰፋፊ ሥራዎች በመምሪያው በኩል እየተከናወኑ እንዳሉም ይገልጻሉ።

እንደ ኃላፊው ማብራሪያ፤ የሐዋሳ ከተማ አስተዳደር ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ በከተማ ከሚከናወኑ በርካታ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ውስጥ ሴቶችን በማሳተፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እያደረገ ይገኛል።በተለይ ደግሞ በዩ አይ ዲ ፒ በሚደገፈው የኮብል ስቶን መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ሰፊ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች የሚሳተፉ ሲሆን፤ በዚህ ሥራ ውስጥ ሴቶች ሃምሳ ከመቶ እንዲወዳደሩ በማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

በብዛት ሴቶች ያሉባቸው ማህበራት ተወዳድረው አሸናፊ እንዲሆኑ የማድረግ ስራዎችን በመስራት በርካታ ሴት ወጣቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ተችሏል።

በሌሎች ፕሮጀክቶችም ድጋፍ በማድረግ የተለያዩ ጨረታዎች ሲወጡ ቅድሚያ ለሴቶች በመስጠት ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሰፋፊ ሥራዎች ተሰርተዋል።በዚህም በርካታ ሞዴል የሆኑ ማህበራት ተፈጥረዋል።በተለይ በኮብል ስቶን መንገድ ሥራና በሼዶች ውስጥ ገብተው በአገልገሎትና በንግድ ዘርፎች ውስጥ የተሰማሩ ማህበራት ራሳቸውን በማብቃት ረገድ ትልቅ ደረጃ ደርሰዋል።

በዚህ በጀት ዓመት በኮብል ስቶን መንገድ ሥራ ከ200 ሺህ በላይ ወጣቶች የዚህ እድል ተጠቃሚ ሲሆኑ፤ ከዚህ ውስጥ ከሀምሳ ከመቶ በላይ የሚሆኑት ሴት ወጣቶች ናቸው።

ሴቶች በኮንስትራክሽን ዘርፍ ተሳታፊ ሆነው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ በዘለለ መብታቸውን እንዲጠቀሙ በማድረግና በማብቃት ተጨማሪ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።ከዩ አይ ዲ ፒ በሚመደብላቸው በጀትም ሴቶች የተለያዩ ስልጠናዎችን ወስደው ራሳቸው አዘጋጅተው ራሳቸው እንዲሸጡ እየተደረገ ይገኛል።ከዚህ ባለፈ የሲ አይ ፒ እቅድ ዝግጅት ላይ ሴቶች ለብቻቸው እንዲወያዩ፣ እንዲወስኑ፣ ለየትኛው ፕሮጀክት ቅድሚያ መሰጠት እንዳለበትና ፕሮጀክቱ ሲያልቅ ምን ያህል ሴቶች ተጠቃሚ እንደሚሆኑና መሳተፍ እንዳለባቸው በመምሪያው በኩል ሰፊ ሥራ ተሰርቷል።

በከተማና መሰረተ ልማት ሚንስቴር የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ዳይሬክቶሬት ከፍተኛ ባለሞያ የሆኑት ወይዘሮ መብራቴ አሰፋ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ በሴቶች ዙሪያ የወጡ አዋጆች፣ ደምቦችና መመሪያዎች በአብዛኛው ክፍተት ያለባቸው ናቸው።ከዚህ አንፃር ሴቶች ከመሬት ጋር በተያያዘ ያሉ ህጎችን፣ ደምቦችንና መመሪያዎችን በመገንዘብ ለሌሎች ሴት እህቶቻቸው ማስተማር አለባቸው።

በመመሪያው መሰረት ሴቶች ከመሬት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግም መሬት አዋጅ፣ ደምብና መመሪያ ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ ሊያሰፉ ይገባል።በተለይ ደግሞ የመሬት ምዝገባ ጥቅሙ ምን እንደሆነና ወደፊት መሬትን በሚገባ አስመዝግቦ ከቤተሰቦቻው ጋር ለሚሰሩ የጋራ ሥራዎች ግንዛቤው እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።ስለመሬት ጉዳይ ሴቶች ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው፤ ተሳታፊም ተጠቃሚም እንዲሆኑ ለማድረግም በርካታ ተግባራትን መከወን ይጠይቃል።

ባለሞያዋ እንደሚገልፁት፤ የሚንስቴሩ የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ከመሬትና መሬት ነክ ጉዳዮች ጋር በመቀናጀት ስለመሬት የሚወጡ አዋጆችን፣ ደምቦችንና መመሪያዎችን ከመሬት ከፍል በመውሰድ ሴቶች በመብቶቻው ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሥራዎች ይሰራሉ።በአብዛኛው ሴቶች ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዙ መድረኮች ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ ሃሳባቸውን እንዲያጋሩ ለመብቶቻውም እንዲሟገቱ የማደረግ ሥራዎችም ይከናወናሉ።

ከታች ጀምሮ በቢሮ ደረጃ ያሉ ሴቶች በመሬት ዙሪያ እምብዛም ግንዛቤ የሌላቸው በመሆኑና አዋጆችን፣ ደምቦችንና መመሪያዎችንም ስለማያውቁ በዚህ ረገድ ግንዛቤኖሯቸው እንዲጠቀሙ ለማድረግም እየተሰራ ነው።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ኃይለማርያም ወንድሙ

በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን፤ 1957 ዓመት የታተሙትን ጋዜጦቻችንን አይተናል። በአዋሽ ሰባት ኪሎ ያለፈቃድ ሣላ ስለገደለው ጣልያናዊ ቱሪስት፤ በወቅቱ ግማሽ ሚሊየን የተባለው የአዲስ አበባ ነዋሪ በቀን 20 ሺህ ሜትር ኩብ ውሃ እንደሚጨርስ እና በቦርከና ወንዝ ላይ የተሠራ ድልድይ ለትራፊክ ክፍት ስለመሆኑ የሚያካትት ዜና ይዘናል።

### ጣልያኑ ያፈቃድ በማደኑ ፫፻ ብር ተቀጣ

ናዝሬት፤ ሲኞር ዳኮር ጆርጅ የተባለ ኢጣሊያዊ ተወላጅ ፤ሚያዝያ ፲፯ ቀን አዋሽ ሰባት ኪሎ መንገድ ሔዶ የአደን ፈቃድ ሳይኖረው፤ አንድ ሳላ ገድሎ ቀንዱን ይዞ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ፤ በወለንጪቲ ፖሊሶችና በደን ዘበኞች ተቆጣጣሪነት ስለተያዘ፤ የየረርና ከረዩ አውራጃ ግዛት ፍርድ ቤት በዓቃቤ ሕግ ሻምበል ተፈራ ደነቀ አማካይነት ተከሶ፤ ፫፻ ብር መቀጫ ከፍሏል። የተያዘውም የሣላ ቀንድ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ተወስኗል።

( ሰኔ 3 ቀን 1957 ዓ.ም የታተመው አዲስ ዘመን)

### ፻፹፫ሺህ፫፻፶፭ ብር የፈጀው የቦርከና ወንዝ ድልድይ ሥራውን ጀመረ

በወሎ ጠቅላይ ግዛት ኮምቦልቻ አጠገብ የሚገኘው የቦርከና ወንዝ ድልድይ ተፈጽሞ ለትራፊክ አገልግሎት የተከፈተ መሆኑን የአውራ ጐዳና ባለሥልጣን የማስታወቂያ ክፍል ገልጧል።

ይኸው አዲስ የተሠራው ድልድይ ፶ ሜትር ርዝመትና ሰባት ሜትር ስፋት ሲኖረው፤ ፩፻፹፫ሺህ፫፻፶፭ ብር ፈጅቷል። በሥፍራው የነበረው የቀድሞ ድልድይ ባለፈው ክረምት በጐርፍ ኃይል መፍረሱ ይታወሳል። ይህንኑ ድልድይ እንደገና ለመሥራት የአምስት ወር ጊዜ የፈጀ ሲሆን እስከዛሬ ከተሠሩት ዘመናዊ ድልድዮች አንዱ ነው ሲል ይኸው የማስታወቂያ ክፍል በድጋሚ አረጋግጧል።

( ሰኔ 3 ቀን 1957 ዓ.ም የታተመው አዲስ ዘመን)

### የአዲስ አበባ ሕዝብ በቀን ፳ ሺህ ሜትር ይጨርሳል

በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆነው ግማሽ ሚሊዮን ሕዝብ በየወሩ ፳ ሺህ ሜትር ኩብ ውሃ የሚጠጣ መሆኑን የአዲስ አበባ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የውሃ ክፍል ዳይሬክተር በሰጡት ወሬ ለመረዳት ተችሏል።

ውሃ ቤታቸው እንዲገባላቸው የሚጠይቁት ሰዎች ብዛት በወር ከ፪፻ እስከ ፬፻ ይደርሳል። የጠያቂዎቹ ብዛት እየጨመረ በመሄዱ የውሃ ክፍሉ ቆጣሪ አልቆበት ከውጭ አገር ለማስመጣት አስቧል። ቆጣሪው እስከ ሐምሌ ወር መጨረሻ ድረስ ስለሚመጣ፤ ሕዝቡ ቅሬታ ሊሰማው አይገባውም። የውሃ ክፍል የሕዝቡን ፍላጐት አሟልቶ ለመያዝ የሁልጊዜ ጥረቱ ስለሆነ ቅሬታ መፈጠር የለበትም ሲሉ ዳይሬክተሩ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ሕንፃ ለሚሠሩ ሁሉ አሸዋ ለሚያጠጡት ሸክላ የሚሠሩትና ከባድ ሥራ የሚያከናውኑት በዚሁ በተጣራ ንጹሕ ውሃ በመሆኑ ዳይሬክተሩ ቅር ተሰኝተዋል። ሕንፃ ሠሪዎች የሆኑ ሁሉ በጉድጓድ ውሃ ቢሠሩና የቧንቧን ውሃ ለመጠጥ ብቻ ቢያደርጉ ከፍ ያለ ዕርዳታ መሆኑን ገልጠዋል። በአሁኑ ጊዜ የአዲስ አበባ የውሃ ደንበኞች ከ፴፩ሺህ በላይ ደርሰዋል።

በገፈርሳ ውሃ ላይ ተጨማሪ እንዲሆን የታሰበው ሁለተኛው ገፈርሳ ሥራውን ከሁለት ዓመት በኋላ እንደሚጀምር ተገልጧል። ይኸውም አዲሱ ገፈርሳ ፲ሚሊዮን (አሥር ሚሊዮን)ሜትር ኩብ የሚይዝ ሲሆን፤ ከአሁኑ ገፈርሳ ጋር ፲፯ ሚሊዮን(አሥራ ሰባት ሚሊዮን) ሜትር ኩብ ፤የከተማውን የውሃ ችግር ከመቼውም የበለጠ ሊያቃልል እንደሚችል ተነግሯል። ይሁን እንጂ አሁንም ቢሆን በከተማው ሕዝብ ላይ ምንም ዓይነት የውሃ እጦት አይታይም።

የአዲሱ ገፈርሳ ግድብ ማጣሪያ ፲፮ ሚሊዮን ፹፫ሺህ ፰፻፭ (አሥራ ስድስት ሚሊዮን ሰማንያ ሦስት ሺህ ስምንት መቶ አምስት ብር) ይፈጃል። በጨረታውም የጀርመን፤ የኢጣልያ፤ የእንግሊዝና የፈረንሳይ አገር ሰዎች እንደሚወዳደሩ በወሬው ተመልክቷል።

የአዲሱ የገፈርሣ ውሃ ግድብ ቢበዛ እስከ መስከረም ፲፱፷ ዓ.ም ድረስ ከቆየ በኋላ ከዚያ ለጨረታው አሸናፊ ሥራው የሚሰጥ መሆኑን ዳይሬክተሩ አብራርተዋል።

በየቦታው ውሃ በእንሥራ ለሚቀዱ በአንድ ሣንቲም ሒሳብ ያስከፍላል። አንዱን ሜትር ኩብ በ፴ ሣንቲም ሒሳብ ያስከፍላል። በየቤቱ ያሉት ግን ለአንድ ሜትር ኩብ ውሃ ፶ ሳንቲም የሚከፈል መሆኑ ታውቋል።

አዲሱ የገፈርሣ ሥራ እስካለቀ ድረስ ለሕዝቡ የሚያገለግል አንድ በጣም ጥልቅ የውሃ ጉድጓድ በቅርቡ ይቆፈራል።

( ሰኔ 5 ቀን 1957 ዓ.ም የታተመው አዲስ ዘመን)

# ዓለም አቀፍ



## ፕሬዚዳንት ባይደን የመሣሪያ ቁጥጥር ሥምምነቱ በአስቸኳይ እንዲተገበር አሳሰቡ

አዲስ አበባ ፡ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን የመሣሪያ ቁጥጥር ሥምምነት ማዕቀፉ በአስቸኳይ እንዲተገበር አሳሰቡ፡፡

የአሜሪካ ምክር ቤት ሴናተሮች በቀረበው የመሣሪያ ቁጥጥር ማዕቀፍ ላይ ተስማምተዋል።

ይህን ተከትሎም ፕሬዚዳንቱ ሕግ አውጪዎች የመሣሪያ ቁጥጥር ማሻሻያውን በፍጥነት ወደ ነጩ ቤተ መንግስት እንዲልኩ ማዘዛቸውን ሲ ጂ ቲ ኤን ዘግቧል፡፡

የአሜሪካ የተወካዮች ምክር ቤት ባለፈው ሳምንት የመሣሪያ ቁጥጥር ረቂቅ ደንብን በአብልጫ ድምፅ ማሳለፉ የሚታወስ ነው።

ረቂቁ ሰዎች መሣሪያ መግዛት የሚችሉበትን ዕድሜ ከ18 ወደ 21 ከፍ እንዲል ይደነግጋል።

መሣሪያ እንዲገዛ ዕድሜው የሚፈቅድለት ማንኛውም ሰው ከ15 ተተኳሽ ጥይቶች በላይ የሚይዝ የጥይት መጋዘን መግዛት እንደማይችልም በወጣው ደንብ ተደንግጓል፡፡



## የሩሲያ ጦር የዩክሬንን ትልቅ የጦር መጋዘን ማውደሙ ተሰማ

አዲስ አበባ፤ የሩሲያ ጦር የምዕራባውያን የጦር መሳሪያዎች ይገኙበታል የተባለን የዩክሬን ትልቅ የጦር መሳሪያ መጋዘን ማውደሙ ተሰማ ፡፡

ኢንተርፋክስ የሩሲያ መከላከያ ሚኒስቴርን ጠቅሶ እንደዘገበው የሩሲያ ኃይሎች በዩክሬን ተርኖፒል ክልል የሚገኘውን የአሜሪካ እና የአውሮፓ ጦር መሳሪያ ይገኝበታል የተባለ መጋዘን በካሊብር ሚሳኤል አውድመዋል፡፡

በተጨማሪም ሶስት የዩክሬን ሱ 25 ተዋጊ ጄቶች ዶኔስክ አቅራቢያ መተው መጣላቸውን የሩሲያ መከላከያ ሚኒስቴር አስታውቋል ሲል ቲ አር ቲ ዘግቧል፡፡

109ኛ ቀኑን የያዘውን የሩሲያ እና የዩክሬን ጦርነት ተጽዕኖ በዓለም ኢኮኖሚ ላይ መታየት መጀመሩን መረጃዎች ያመላክታሉ።

በአገራቱ መካከል የሰላም ድርድር ጥረቶች ሲደረጉ ቢቆይም የሚታይ ውጤት ማምጣት እንዳልተቻለም ዘገባዎች ያስረዳሉ፡፡

ምዕራባዊያን አገራት ለዩክሬን የሚያደርጉትን የጦር መሳሪያ ድጋፍ አጠናክረው መቀጠላቸው ደግሞ ጦርነቱን ይበልጥ አባብሶታል በሚል አንዳንድ አገራት ስጋታቸውን እየገለጹ ይገኛሉ፡፡

# ስፖርት

## በአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና 5ኛ ሆኖ ያጠናቀቀው ቡድን ዛሬ ይሸለማል

**ቦጋለ አበበ**

ለአምስት ተከታታይ ቀናት በሞሪሽየስ አዘጋጅነት ሲካሄድ ቆይቶ ከትናንት በስቲያ በተጠናቀቀው ሃያ ሁለተኛው የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኢትዮጵያ አምስተኛ ደረጃን ይዛ አጠናቃለች። በቻምፒዮናው በ4 ወርቅ፣ 6 ብርና 4 ነሃስ በአጠቃላይ 14 ሜዳልያ መሰብሰብ የቻለው የኢትዮጵያ ልኡካን ቡድን ዛሬ ወደ አገሩ ሲመለስ በአራራት ሆቴል በሚደረግለት የአቀባበል መርሃግብር ላይ እንደሚሸለም ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

ኢትዮጵያ ከሃምሳ በላይ አትሌቶችን በአጭር፣ መካከለኛና ረጅም ርቀቶች፣ በ3ሺ ሜትር መሰናክል፣ በርምጃና በሜዳ ተግባራት ውድድሮች በቻምፒዮናው አሳትፋለች። በዚህም አትሌት ሞገስ ጥኡማይ በወንዶች 10ሺ ሜትር የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ ማስመዝገብ የቻለ ሲሆን ጭምዴሳ ደበሌ በዚሁ ውድድር የብር ሜዳሊያ ማጥለቅ ችሏል። በወንዶች 3ሺ ሜትር መሰናክል ኃይለማርያም አማረ የወርቅ ሜዳሊያ ሲያስመዘግብ ታደሰ ታከለ በዚሁ ውድድር የብር ሜዳሊያውን ወስዷል። አትሌት ኃይለማርያም አማረ በቻምፒዮናው የመጨረሻ ቀን ውድድርም በ5ሺ ሜትር ሁለተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ በማጥለቅ በሞሪሽየስ አስደናቂ ጊዜን ማሳለፍ ችሏል። አራተኛው የወርቅ ሜዳሊያ በሴቶች 3ሺ ሜትር መሰናክል በአትሌት የወርቅውሃ ጌታቸው ሲመዘገብ በዚሁ ውድድር ዘርፌ ወንድማገኝ የብር ሜዳሊያ ማጥለቅ ችላለች።

በሴቶች ስምንት መቶ ሜትር አትሌት ነጻነት ደስታ የብር ሜዳሊያ ያስመዘገበች ሲሆን በሴቶች 5ሺ ሜትር በተመሳሳይ አትሌት ፋንታዬ በላይነህ የብር ሜዳሊያ ማጥለቅ ችላለች። በ20 ኪሎ ሜትር የሴቶች ርምጃ ውድድር አትሌት የኋልዬ በለጠው ተጨማሪ የብር ሜዳሊያ ስታስመዘግብ በተመሳሳይ የወንዶች ውድድር አትሌት ዮሐንስ አልጋው የነሐስ ሜዳሊያ ማጥለቅ ችሏል። በሴቶች 10ሺ ሜትር መሰረት ገብሬ፣በ1500 ሜትር ሴቶች አያል ዳኛቸው፣1500 ሜትር ወንዶች አዳነ ካሳይ የነሐስ ሜዳሊያ ያስመዘገቡ አትሌቶች ናቸው።



አትሌት ኃይለማርያም አማረ በ3ሺ መሰናክልና በ5ሺ ሜትር ሁለት ወርቅ በማጥለቅ በቻምፒዮናው ደምቆ ታይቷል፣

ኬንያውያን አትሌቶች ለበርካታ አስርት ዓመታት በአፍሪካም ይሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ የ3ሺ ሜትር መሰናክል ውድድሮች በሁለቱም ጾታ ፍጹም የበላይነት እንዳላቸው ይታወቃል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን ይህ ታሪክ በግል ውድድሮች ጭምር እየተገለበጠ እንደመጣ በርካታ ማሳያዎች አሉ። በ22ኛው የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ሞሪሺየስ ላይ በርቀቱ የተመዘገበው ውጤትም አንዱ ማሳያ ሆኗል። ኢትዮጵያውያን በሁለቱም ጾታ በርቀቱ የወርቅና የብር ሜዳሊያዎችን በማጥለቅ የኬንያውያን ባህል የሆነውን ውድድር እየወረሱ እንደሚገኙ አስመስክረዋል።

በዚህ የአፍሪካ ቻምፒዮና በርምጃ ውድድሮች በሁለቱም ጾታ የተመዘገቡ ውጤቶችም ለኢትዮጵያ አበረታች ሆነው የተጠቀሱ ሲሆን ባልተለመዱ ርቀቶችም በርካታ የዲፕሎማ ውጤቶች ተመዝግበዋል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ አሁንም ባልተለመዱ ርቀቶችና ውድድሮች ወደ ውጤታማነት መምጣቷ አበረታች የመሆኑን ያህል ውጤታማ በሆነችባቸው ርቀቶች ውጤቷ እየሳሳ መሄዱ አሳሳቢ እንደሆነ በሞሪሺየሱ ቻምፒዮና ታይቷል። ኢትዮጵያ ውጤታማ ባልነበረችባቸው ርቀቶች አዳዲስ ክብሮችን የማሳካቷን ያህል ቀድሞ ውጤታማ በሆነችባቸው ውድድሮች በጥንካሬዋ ብትቀጥል ምናልባትም በዚህ የአፍሪካ ቻምፒዮና የተሻለ ውጤት ይዛ የማጠናቀቅ እድል ይኖራት ነበር። ያም ሆኖ አሁን የተመዘገበው ውጤት ቀላል ቦታ የሚሰጠው አይደለም።

በአጠቃላይ በሃያ ሁለተኛው የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ኬንያ ባህሏ የሆነው የ3ሺ ሜትር መሰናክል ውድድርን በሁለቱም ጾታ በኢትዮጵያ የበላይነት ቢወሰድባትም 10 ወርቅ፣ 5 ብር፣ 8 ነሐስ በአጠቃላይ 23 ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ ቀዳሚውን ደረጃ ይዛ አጠናቃለች። ደቡብ አፍሪካ በ9 ወርቅ፣ 13 ብር፣ 14 ነሐስ በአጠቃላይ በ36 ሜዳሊያዎች ሁለተኛ ሆና አጠናቃለች። 5 ወርቅ፣ 3 ብር፣ 3 ነሐስ በአጠቃላይ 11 ሜዳሊያ የሰበሰበችው ናይጄሪያ ሶስተኛ ደረጃን ይዛ ጨርሳለች። አልጄሪያ ከኢትዮጵያ በልጣ ለማጠናቀቅ 5 ወርቅ፣ 3 ብር፣ 1 ነሐስ በአጠቃላይ 9 ሜዳሊያ መሰብሰብ ችላለች።


## የግልጽ እና ሐራጅ ጨረታ ማስታወቂያ

የጉምሩክ ኮሚሽን ጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት በኮንትሮባንድ የተያዙ የተለያዩ ኤሌክትሮኒክስ፤የቤት ማስዋቢያ፤ ህንፃ መሳሪያ፤ አልባሳት የቤት ዕቃ፣ እስፔርፓርትስ፣ ልዩ ልዩ በሃራጅ እና በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡ ፡ስለዚህ ለጨረታ የቀረቡትን ዕቃዎች ከ7/10/2014 ዓ.ም ጀምሮ በማየት እና ከዚህ ቀጥሎ የተገለፁትን መስፈርቶች በማሟላት መወዳደር የምትችሉ መሆኑን ቅ/ጽ/ቤቱ ይገልፃል፡፡

**በጨረታው ሳይ ስመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች፡-**

1. በዘርፍ የፀና ንግድ ፍቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት ያለው ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፣
2. ለሃራጅ ጨረታው 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ሲፒኦ /CPO/ ለግልጽ ጨረታ የመጫረቻውን 5% (ፐርሰንት) ማስያዝ የሚችል፡፡
3. ተጫራቹ ለሃራጅ የሚገዛበትን መነሻ ዋጋ እራሱ ያቀርባል፣
4. ለግልጽ ጨረታ ቅ/ጽ/ቤቱ ካስቀመጠው መነሻ ዋጋ ተነስቶ ዋጋ በመሙላት በተቀመጠው ሳጥን ውስጥ ማስገባት የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡
5. ተጫራቹ በጨረታው አሸንፎ የገዛውን ዕቃ ወዲያውኑ ከፍሎ በ05 ቀን የሚረከብ መሆን አለበት፣
6. ዕቃዎቹን አሸንፎ የገዛ ተጫራች የሚፈለግበትን ዋጋ ወዲያውኑ ከፍሎ በ05 ቀን ውስጥ ካልተረከበ ያስያዘው ሲፒኦ ለመንግስት ገቢ ይሆናል፣
7. በጨረታው ያላሸነፉት ተጫራቾች ያስያዙት ሲፒኦ ወዲያውኑ ይመለስላቸዋል፡፡
8. ማንኛውም ተጫራች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጅጅጋ ቅርንጫፍ ሲፒኦ /CPO/ አሰርቶ ማምጣት አለበት፡፡
9. አሳማኝ የሆነ ምክንያት ከተገኘ እና በመ/ቤቱ ተቀባይነት ካላገኘ ጨረታውን መሰረዝ ይችላል፡፡
10. ማንኛውም ተጫራች ዕቃዎቹን ካሸነፉ በኋላ ከጅጅጋ ውጪ ለማጓጓዝ ቢፈልግ እንደቦታው ርቀት በቀነ ገደብ መሸኛ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡
11. ተጫራቹ ዕቃዎቹን አሸንፎ ከተረከበ በኋላ መሸኛ ሳይዝ የትም ቦታ ቢያዝ መ/ቤቱ ኃላፊነቱን አይወስድም፡፡
12. ተጫራቾች የሞሉትን የጨረታ ሰነድ ሰኔ 11/10/2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡00 እስከ 3፡45 በጅግጅጋ ጉ/ኮ/ቅ/ጽ/ቤት በተዘጋጀ የጨረታ ማስገቢያ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ጨረታው 3፡45 ተዘግቶ በ11/10/2014 ዓ.ም ከረፋዱ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የሚከፈት ይሆናል፡፡
13. የሃራጅ ጨረታው የሚካሄደው 11/10/20114 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት በመሰብሰቢያ አዳራሽ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይሆናል፡፡

N.B አሸናፊው ተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ 15% ፐርሰንት የሚከፍል መሆኑ ይታወቅ፡፡

**በጉምሩክ ኮሚሽን የጅጅጋ ቅ/ጽ/ቤት**

## የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ የግዥ መለያ ቁጥር- መከ/ኮም/ስፔ/ሆ/ል/ኮ/ል/ግ/ጨ-01/2014

መከላከያ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለ2015 ዓ.ም በጀት ዓመት

* ከአዲስ አበባ ቢሾፍቱ ደርሶ መልስ እና በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ቢሾፍቱ ከተማ ዙሪያ ደርሶ መልስ ለክፍሉ ሰራተኞች የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጡ የተለያዩ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ከአከራይ ድርጅቶች መከራየት
* ለህሙማን ቀለብ አገልግሎት የሚውል አትክልትና ፍራፍሬ ፣ የስጋ ፣ የወተት ተዋፅኦ ፣ የባልትና ውጤቶች በዘርፉ ከተሰማሩ አቅራቢ ድርጅቶችን በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ አመወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፤

**ዝርዝር መስፈርቶች በሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ሳይ ይገለፃሉ፡፡**

1. ተጫራቾች የዘመኑን የታደሰ ንግድ ስራ ፍቃድ ፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት /አላይን/ ፣ የቫት /ተጨማሪ እሴት ታክስ/ ፣ ቲን ነበር /የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/ ፣ በጨረታ እንዲሳተፉ የሚገልፅ፣ የዘመኑን ግብር በአግባቡ የከፈሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ /ታክስ ክሊራንስ/ እና ሌሎችም ከጨረታው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ዶክመንቶች ማቅረብ የሚችሉ የተጠቀሱትን ሰነዶች ማስረጃ ፎቶ ኮፒውን ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር አያይዘው የሚያቀርቡና ዋናውን ሲጠየቁ ማቅረብ የሚችሉ፤
2. ጨረታው የሚከናወነው በግልፅ ጨረታ ሥነ-ሥርዓትና ይህንን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲ ሪፐብሊክ መንግስት ባወጣው የመንግስት የግዥ አዋጅ መሠረት ይሆናል፡፡
3.በመኪና ኪራይ አገልግሎት ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የማይመለስ የኢትዮጵያ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) ብቻ በመክፈል የተዘጋጀውን የጨረታ ሰንድ መውሰድ ይችላሉ፤
4. ለህሙማን ቀለብ አቅርቦት ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የማይመለስ የኢትዮጵያ ብር 150.00 (አንድ መቶ ሀምሳ ብር) ብቻ በመክፈል የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ መውሰድ ይችላሉ፡፡
5. ተጫራቾች ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የመወዳደሪያ ሰነዳቸውን ለዚሁ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይችላሉ፤
6.የጨረታ ሳጥኑ በ23/10/2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዚሁ ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት ተኩል ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ23/10/2014 ዓ.ም ይከፈታል፤
7. ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ቅዳሜን ጨምሮ ለ15 (አስራ አምስት) ቀናት አየር ላይ የሚቆይ ሲሆን በ15ኛው (አስራ አምስት) ቀን ጨረታው ይከፈታል፤
8. በመኪና ኪራይ አገልግሎት ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን ብር 60,000.00 (ስልሳ ሺህ ብር) ብቻ በመከላከያ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በC.P.O ማስያዝ አለባቸው፡፡
9. በህሙማን ቀለብ አቅርቦት ለመሳተፍ ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን ብር 40,000.00 (አርባ ሺህ ብር) ብቻ በመከላከያ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ስም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በC.P.O ማስያዝ አለባቸው
10. መስሪያ ቤቱ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፤
11. ሰነዱ ወጪ የሚሆንበት እና ጨረታው የሚከፈትበት አድራሻ- ደብረ ዘይት ቢሾፍቱ ቀበሌ 05 ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አጠገብ መከላከያ ኮም/ስፔ/ሆ/ል ቢሮ ቁጥር 639 ስልክ ቁጥር 09 20 43 42 29/ 09 29 19 08 52

**የመከላከያ ኮምፕሬሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል**